# ክርስቲያን እና ፖለቲካ

## በፖለቲካ ሂደት ውስጥ የሚኖረው
## የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ተሳትፎ

በኤልያስ በቀለ

ሐምሌ 1996 ዓ.ም

# CHRISTIAN AND POLITICAL PARTICIPATION

© 2004 by Elias Bekele

የመጀመሪያ እትም ሐምሌ 1996 ዓ.ም

አሳታሚና አከፋፋይ፡- የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
ስልክ 51 29 73፥ 49 32 52፥ 71 11 73
ፋክስ - 51 12 42
ኢ-ሜይል፡ SIMmedia@telecom.net.et

# ማውጫ

ገጽ

## ክፍል አንድ

1. መንግሥትና የሥልጣን ምንጩ ........ 1
2. ፖለቲካ ምንድን ነው? ........ 2
3. የመንግሥት አመጣጥና አስፈላጊነት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ........ 4
4. የመንግሥታት ዐይነት ከእግዚአብሔር አሳብ አንጻር ........ 6
   - ቶታሊቴሪያን መንግሥት ........ 7
   - አናርኪ /መንግሥት አልባ/ ........ 8
   - ዲሞክራሲ ........ 9
5. የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ........ 10
   - የካቶሊኮች አመለካከት ........ 13
   - የአናባፕቲስቶች አመለካከት ........ 14
   - የሉተራንና የካልቪኒስቶች አመለካከት ........ 15
6. በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖሩ የሚችሉ ግንኙነቶች ........ 16
7. ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት የምታበረክተው አገልግሎት ........ 24

ማጠቃለያ አሳብ ........ 42

## ክፍል ሁለት ........ 43

### ክርስቲያንና ፖለቲካ ........ 43

1. ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ስለመሳተፉ የሚሰጡ አስተያየቶች ........ 43
2. ክርስቲያን ሊሳተፍባቸው የሚገቡ የፖለቲካ ሂደቶች ........ 47
3. የፖለቲካ ሥልጣን የያዘ ክርስቲያን ሊከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች ........ 52
4. በፖለቲካ ውስጥ ለሚሳተፍ አማኝ የቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ........ 55

ማጠቃለያ አስተያየት ........ 57

BIBLIOGRAPHY ........ 58

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ለአንባብያን እንዳቀርብ ቸርነቱ ላልተለየኝ የጅማሬዬና የፍጻሜዬ ባለቤት ለሆነው አምላኬና ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባውን ክብርና ምስጋና እሠዋለሁ። በተጨማሪም ይህ ጽሑፍ ለአንባብያን ሊደርስ የቻለው በባለቤቴ በወ/ሮ አለማሽ አለሙና በልጆቼ አቢግያ፣ ነቢዩና ሩት ያልተቋረጠ ድጋፍ በመሆኑ ለእነርሱም የማቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ ነው።

በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ እንድነሣሣ የሐሳቡ ጠንሳሽ የሆነችውን ወ/ሮ ሶፍያ ሙሉን ከልብ ላመሰግናት እወዳለሁ። ጊዜዋን መሥዋዕት አድርጋ ባለመሰልቸት ይህንን ጽሑፍ በኮምፒውተር በመጻፍ ለረዳችኝ ለወ/ት ማሩት ሰይፉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ዓላማዬ ከግቡ እንዲደርስ የሐሳብና የጸሎት ድጋፋቸውን ለለገሱኝ ወንድሞች ለዴቪድ ካሣ፣ ለፀጋዬ ጳውሎስ፣ ለመሐመድ ሀሰንና ለአሰፋ የሺጥላ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም የአይ.ኢ.ሲ. (IEC) የአምልኮ ጓድ መሪ ጂኒ ሆልት (Ginny Holt) እና አባላቱ በሙሉ ምኞቴ ከዳር እንዲደርስ ላሳዩኝ ድጋፍ እግዚአብሔር ይስጣችሁ ለማለት እወዳለሁ። በመጨረሻም በተለያየ መንገድ ለዚህች መጽሐፍ ዕውን መሆን የረዱኝን ሰዎች ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

# የአሳታሚው ማስታወሻ፥

ወደ ኋላ መለስ ብለን የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት፥ ክርስቲያኖች ከወንጌል ምስክርነት (ስብከት) ባሻገር በኅብረተሰቡ ውስጥ ይታዩ የነበሩትን አስከፊ ገጽታዎች ሁሉ ለመለወጥ ይታገሉ እንደነበረ እንረዳለን። በእንግሊዝና በአሜሪካ ከተካሄዱ ታላላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች በኋላ (ቀጥሎ) ታላላቅ ማኅበራዊ ለውጦች ተከናውነዋል። ለምሳሌም ያህል የባሪያ ንግድ መወገድንና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ነገር ግን ይህ የወንጌል ስብከትና የማኅበራዊ ለውጥ እንቅስቃሴ ጥምረት ያለ ውጣ ውረድ የዘለቀ አልነበረም። አልፎ አልፎ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ችላ ያሉባቸው ወቅቶችም ነበሩ።

ለእያንዳንዱ ሰው ወንጌልን የመስበኩን ቀዳሚነት ሁላችንም እናምንበታለን። ከዚህ ጋር ጎን ለጎን የወንጌላውያን አማኞች ማኅበራዊ ተሳትፎ ችላ እንዳይባል እያሳሰብን፥ ሁሉም ወንጌላውያን አማኞች ለሰው ዘር እኩልነት፥ ነጻነትና ሁሉም ዓይነት ማኅበራዊ ፍትሐዊነት እንዲሟገቱ እንማጸናለን።

ይህንንም እንዴት እንደምናከናውን የአቶ ኤልያስ በቀለ ዝግጅት ጥቆማዎችን ይሰጠናልና አንብባችሁ ትጠቀሙበት ዘንድ እንጋብዛችኋለን። ይህ መጽሐፍ የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ከትርጉም ሥራዎች ይልቅ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ጸሐፊዎችን ለማበረታታት ከ1992 ዓ.ም ወዲህ የጀመረው ጥረት አካል መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን። ይህም በዚህ መልክ ከተስተናገዱት አምስተኛው መጽሐፍ ሲሆን፥ ለዚህ ያበቃንን እግዚአብሔር አምላካችንንም እናመሰግናለን። መልካም ንባብ!

ዘነበ ገብረሐና

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

ሥራ አስኪያጅ

# መቅድም

ክርስትና ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት ግንኙነት ላይ ሲንጸባረቅ የቆየው የክርስቲያኖች አመለካከት ብዙ ልዩነት የታየበት ነው። ይህ በዘመን ሁሉ የውይይት ርእስ ሆኖ የኖረ ጉዳይ ክርስቲያን ጠበብትን ያወዛገበ፣ በውይይትም ተብላልቶ ወደ አንድ ማስማሚያ አሳብ ሊመጣበት ያልተቻለ ሆኖ ቆይቷል። መፍትሔ ተብለው የተሰነዘሩ አሳቦች ሌላ የልዩነት መድረክ፣ ሌላ ንትርክ ሲፈጥሩ እንጂ ወደ አንድ የጋራ አመለካከት ሲያመጡ አልታዩም። ከእነዚህ ሊታረቁ ካልቻሉ አመለካከቶች ውስጥ ማብቂያ የሌለው ንትርክና ሁለት ጽንፈኛ (extrems) አመለካከቶች ብቅ አሉ። በአንደኛው ጽንፍ ያለው አቋም፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ የሁሉ በላይ እና ጌታ በመሆኑ፣ ክርስቲያኖች ምድራዊ ተቋማትን ሁሉ መንግሥትንም ጨምሮ በቤተ ክርስቲያን ሥር አድርገው ማየት እና ይህም ተግባራዊ እንዲሆን የመጣር ኃላፊነት አለባቸው የሚል ነው። ይህ አቋም በመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ የበላይነት ጨብጣ በነበረበት ወቅት ገንኖ የነበረ ነው።

በሌላው ጽንፍ ያለው አቋም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ትኩረት ወንጌልን መስበክ፣ የእውነተኛ ክርስቲያኖችም ብቸኛ ትኩረት ውስጣዊና መንፈሳዊ የሆነውን ሕይወታቸውን በቃሉ ኮትኩተው ለሰማያዊ ቤታቸው ማዘጋጀት እንጂ ምድራዊና ዓለማዊ ወደሆነው የኅብረተሰቡ ባሕልም ሆነ ልማድ (culture) እንዲሁም የፖለቲካ ሕይወት መጠጋትም ሆነ ለመደባለቅ መሞከር አይገባቸውም የሚል ነው። እነዚህ ጽንፈኛ አመለካከቶች እንዳሉ ሆነው፥ በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ሌላ መካከለኛ አመለካከት አለ።

ይህ አመለካከት የቤተ ክርስቲያንንና የመንግሥትን ተቋማዊ ልዩነት ይቀበላል፤ ሆኖም ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ክርስቲያኖች በምድር ላይ እንዳሉ የክርስቶስ አምባሳደሮች የሰማያዊው መንግሥት አሳብ የኅብረተሰቡን ተቋማት በሙሉ እንዲለወጡና ለክርስቶስ እንዲገዙ፣ የተበላሹ ግንኙነቶች እንዲፈወሱና የኅብረተሰቡ አካላት በሙሉ መልካም የሕይወት አቅጣጫን እንዲከተሉ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው የሚል ነው። ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው ታላቅ ተግባር ሰዎችን ብቻ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ የሚያበቃና ጠባብ መሠረት ያለው ሳይሆን ሰፊ መሠረት ያለው፣ ዓለምንና በዓለም ላይ ያለውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅና ወደ ቀደመው ክብሩ እርሱም በፈጣሪው ሥር ወደ መገዛት የመመለስ ሥራ የተሠራበት በመሆኑ ነው የሚል ነው።

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ደግሞ ኅብረተሰባችን የገባበት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ምግባራዊ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ችግር ከባድና የሚያስፈራ ቢሆንም፥ ይህንን ለመለወጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና የአማኞች ተሳትፎ በጣም ውሱን ነው። በተለይ ደግሞ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ ያለን ተሳትፎ ከነአካቴውም የለም ለማለት ይቻላል። ለተሳትፎአችን ውሱንነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት ከዚህ የሚከተሉት እንደሆኑ እገምታለሁ። በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ወደ አገራችን በመጡት ሚሲዮናውያን ላይ የነበረው ተጽዕኖ ነው። ለዘመናት የዘለቀውና በሚሲዮናውያን ላይ ያነጣጠረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጥርጣሬና የጥላቻ ዘመቻ ሚሲዮናውያኑ ከመንግሥትና ከፖለቲካ ጉዳዮች ራሳቸውን እንዲያገልሉና በማኅበራዊ ጉዳዮች (Social Action) ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ተጽዕኖ አድርጓል።

ይህም የመገለል ባህልና አመሠራረት ታሪካቸው ከሚሲዮናውያን ጋር ወደ ተቀራኘው የአገራችን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቀደምት መሪዎችና አማኞች ላይ ተዛምቶ በመጤነት እንዲፈረጁና የዜግነት መብታቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት በአገራዊና በመንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ ከማድረግ እንዲቆጠቡ፥ ይብሱንም ባይተዋርነት እንዲሰማቸው አድርጓል። ይህ ሁኔታ ዛሬም ድረስ ቀጥሎ ያለ ሐቅ ነው።

ሌላው ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በሚያስደንቅ ፍጥነት ያደገችበት፣ በዚያው ልክ ደግሞ ከፍተኛ መከራና ስደት፥ እስርና እንግልት የደረሰበት ወቅት በአገዛዙና በሃይማኖት ጭቆናው ወደር በማይገኝለት በደርግ ኮሙኒስታዊ አገዛዝ ዘመን በመሆኑ ስለ መንግሥትና ስለ ፖለቲካ ያለን ግንዛቤ ፅልመታዊ (pessimistic) እንዲሆን አስተዋጽኦ በማድረጉ ነው። ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ፣ ስለ መንግሥትም ሆነ የሥልጣኑ ምንጭ፣ ስለ ፖለቲካና ስለ ዜግነት ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖረን ባለመደረጉ ነው። ይህም፣ ከላይ ያነሣሁትና እስከ አሁን ድረስ ተጽዕኖ እያደረገብን ያለው የመገለል ባህል በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ያጠላው ክፉ ጥላ ባለመገፈፉ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ዝምታን እንዲመርጡ አስገድዷቸዋል።

በእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሣ ውሱን በሆኑ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ስናተኩር ሕዝባዊና መንግሥታዊ በሆኑ ፖለቲካዊና ሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ በራችንን ዘግተን ተቀምጠናል። ይህም ሁኔታ በወንጌላውያን አማኞች ላይ እስከ አሁን ድረስ በጎ አመለካከት በሌላቸው ክፍሎች የአገር ፍቅር የሌለን ዜጎች አድርገው እንዲያሳጡን፣ ስማችንንም በክፉ እንዲያጠፉ ምክንያት ሆኖላቸዋል።

የዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ዓላማም ወንጌላውያን አማኞች በመንግሥትና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ እስካሁን የያዙት የተሳሳተ አቋም እንዲስተካከልና

እንደ ማንኛውም ዜጋ እነርሱም የዜግነት ግዴታቸውን በሁሉም መስክ በተገቢው መንገድ መወጣት እንደሚገባቸው ለማመላከት ነው። የክርስቲያኖች የፖለቲካ ተሳትፎ ሲነሣ አብሮ የሚጠቀስ ነገር ቢኖር በመግቢያዬ ላይ ያነሣሁትና በዘመናት ሁሉ ክርስቲያኖችን ሲያወዛግብ የኖረው ወደ አንድ ማስማሚያ አሳብ ላይም ሊደርሱ ያልቻሉበት፤ አሁንም ድረስ ቢሆን ልዩነቶችን እያስተናገደ ያለ እና የማያባራ ንትርክ ውስጥ የሚከት ርእስ ጉዳይ መሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ የክርስቲያኖችን የፖለቲካ ተሳትፎ በተመለከተ አንዳች ከማለት ይልቅ ጀርባ መስጠቱ ቀላሉና ሙግት የማይጋብዝ አማራጭ ሆኖ ቆይቷል።

ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ ለማቅረብ ስነሣ ሊጫር የሚችለውን ውዝግብ በሚገባ ብረዳም፤ ይህንን ከበድ ያለ ርእስ ጉዳይ አሁን ለማንሣት የተገደድኩት፤ በአንድ በኩል በአማኞች ዘንድ እስከ አሁን ድረስ እየታየ ያለው ነገሮችን በገለልተኝነት የማየት ባህል እንደ ብቸኛ አማራጭ የመወሰዱ ጉዳይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተሳትፎአችን በእጅጉ በመራቁ በአገራችን ላይ ያጠላው ሁለ ገብ  አደጋ አሳሳቢ ሆኖብኝ እንጂ፥ ከእውቀትም ሆነ ካካበቱት ልምድ ተነሥተው በዚህ ጉዳይ ላይ በሳል የሆነ አሳብ መሰንዘር ከሚችሉ ወገኖች የተሻለ እውቀት ኖሮኝ አይደለም። እዚህ ላይ ሊሠመርበት የምፈልገው አንድ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም አገራችን ለገባችበት የመከራ አዘቅት መድኃኒት ለመሆን የአማኞች ተሳትፎ መተኪያ የሌለው መሆኑን በብርቱ ብከራከርም መድኃኒቱ በብቸኝነት የሚገኘው በአማኞች እጅ ነው የሚል አመለካከት ግን የለኝም። ይህ በአገራችን ጉዳይ ላይ ብቸኛ ወኪሎችና ተቆርቋሪዎች አድርገው ራሳቸውን ከሚመለከቱና ሌሎቻችን ግን በመጤነት ከሚፈርጁ ክፍሎች አካሄድ ብዙም የማይርቅ በመሆኑ አጥብቀን ልንሸሸው የሚገባ ጉዳይ ነው።

መጽሐፉ በሁለት የተከፈለ ሲሆን፤ ክፍል አንድ የአገራችን ወንጌላውያን አማኞች መንግሥትንና ፖለቲካን በምን መልኩ መረዳት እንደሚገባቸው ይተነትናል፤ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት በሚገባው የተሳትፎ ዐይነት ላይ አስፈላጊ ነጥቦችን ያነሣል። ክፍል ሁለት ክርስቲያኖች በግላቸው በአገራቸው የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ሊኖራቸው ስለሚገባው ተሳትፎና ለዚህ ተግባር የሚነሡ ደግሞ አስቀድመው ሊገነዘቡት በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ አሳቦችን ይሰነዝራል። ይህ የግል ተሳትፎ ያለ ቤተ ክርስቲያን እገዛ የትም ሊደርስ እንደማይችል እሙን በመሆኑ ይህንን የሚመለከት አሳብ በዚሁ ክፍል ውስጥ ተካትቷል።

# ክፍል አንድ

## 1. መንግሥትና የሥልጣን ምንጩ

መንግሥት የሚለው ጽንሰ አሳብ በሁለት ዐይነት መንገድ ግልጋሎት ላይ ይውላል፤ የመጀመሪያው፣ «መንግሥት» ወይም "State" ሲባል አንድን ተደራጅቶ ያለ ኅብረተሰብን ለማመላከት የሚውል ቃል ሲሆን፥ ገዢዎችም (Rulers) ሆኑ ተገዢዎች (The ruled) በአንድ ላይ ተጠቃልለው የሚጠሩበት ቃል ነው። ሁለተኛው፣ «መንግሥት» ወይም "Govrnment" ሲባል የፖለቲካ ሥልጣን ይዞ አንድን ኅብረተሰብ እንዲያስተዳደር የተደራጀ ተቋም ማለት ሲሆን፥ በገዢነት ተግባር ላይ ያሉትን ብቻ ይወክላል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ «መንግሥት» የሚለውን ቃል በአብዛኛው የምጠቀመው በሁለተኛ ደረጃ እንደተቀመጠው፣ የፖለቲካ ሥልጣንን ይዞ አንድን ኅብረተሰብ የሚያስተዳደር ተልዕኮ ያለውን ተቋም ነው። መንግሥት የማስተዳደር ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት ተገቢ የሆነ ሥልጣን (authority) ስለሚያስፈልገው ይህንኑ የጨበጠ ተቋም ነው። እዚህ ላይ የሚነሣው ዋነኛ ጥያቄ የመንግሥት የሥልጣን ምንጭ ከየት ነው? የሚለው ይሆናል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ዐይነት አመለካከቶች አሉ። አንደኛው፥ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር ነው ሲል፤ ሌላው ደግሞ፥ የሥልጣን ባለቤት ሕዝቡ በመሆኑ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭ ሕዝቡ ነው የሚል ነው።

ወደ እግዚአብሔር ቃል ስንመጣ ግን ሥልጣን የሚገኘው የሥልጣን ሁሉ ባለቤትና ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር እንደሆነ እናያለን (ሮሜ 13፡1፤ ዳን. 4፡25)። እንደ ሙሴና ኢያሱ እንዲሁም እንደ ሌሎቹ የእስራኤል መሳፍንትና ነገሥታት በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከተቀቡት በስተቀር፥ ሰዎች በተለያየ መንገድ ወደ ሥልጣን ሲወጡ ይታያል። በቀድሞ ዘመንም ይሁን አሁን ባለንበት ሰዎች በሦስት መንገድ ወደ ሥልጣን ይወጣሉ። አንደኛው፣ በዘር በሚገኝ የሥልጣን ውርስ ማለትም ከንጉሥ ወደ ልጅ የሚተላለፍ የሥልጣን ዝውውር፤ ሁለተኛው፣ በመፈንቅለ መንግሥት ወይም በዐመፅ የሚገኝ ሥልጣን ሲሆን፤ ሦስተኛው፣ ደግሞ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር መረዳት አለብን፤ ይኸውም በየትኛውም መንገድ ወደ ሥልጣን

ቢመጣም የሥልጣኑ ተቋም (Institution) ምንጩና ባለቤቱ ግን እግዚአብሔር መሆኑን፥ ወደ ሥልጣንም የመጣው መልካምም ይሁን ክፉ ተቋም ከእግዚአብሔር መሆኑን ነው።

ይህንን በሚገባ ለመረዳት ጋብቻን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል። ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር ለመሆኑ የቃሉ ማስረጃ አለን። ጋብቻን ከአመሠራረቱ ጀምሮ ጥሩ ወይም መጥፎ የማድረግ ድርሻ ግን የሰው ነው። የመንግሥት ሥልጣንም እንዲሁ ነው፤ ፈጣሪውና ባለቤቱ ሁሉም በእርሱና ለእርሱ ሊሆንለት የተገባው ክርስቶስ ሲሆን፥ ምን ዐይነት መንግሥት ሊሆንልን እንደሚገባን ማወቅ ግን የእኛ የሰው ልጆች ፋንታ ነው። ለዚህም እንደ ምሳሌ የሚሆነን በመጽሐፈ ሳሙኤል ምዕራፍ ስምንት ላይ እናገኛለን። እግዚአብሔር ለእስራኤል ማለትም ለሕዝቡ የወሰነላቸው የመንግሥት ዐይነት አምላክ ገዛ (Theocracy) ሆኖ ሳለ፥ እነርሱ ግን በዙሪያቸው እንደነበሩት አሕዛብ በንጉሥ መተዳደርን መረጡ። በውጤቱ የሚጎዱት እነርሱ መሆናቸውን እግዚአብሔር ቢያውቅም ምርጫቸው ስለሆነ ግን ንጉሣዊ ሥርዐት እንዲመሠርቱ ፈቀደ። ሆኖም ሥርዐተ መንግሥቱ ቢለወጥም እንኳን፥ ከዚያም በኋላ የመሾምና የመሻር ሥልጣን ብቸኛው ባለቤት እግዚአብሔር ነበር።

ይህ የእግዚአብሔር የማይገሰስ ሥልጣን በእስራኤል ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም፤ ዳንኤል 4፡17፤ ኤርምያስ 27፡5–6፤ ኢሳይያስ 45፡1፤ እና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያስገነዝቡን የአሕዛብ ነገሥታትንም የሚሾምና የሚሽር፤ በፍጥረቱ ሁሉ ላይም የሚያነግሣቸው እግዚአብሔር መሆኑን ነው። ከዚህ የምንማረው ማንኛውም ምድራዊ ባለሥልጣን ፍጹም የሆነ ሥልጣን እንደጨበጠ አድርጎ ራሱን ሊመለከት እንደማይገባው ነው። ምክንያቱም ሥልጣን ሁሉ የውክልና ሥልጣን በመሆኑ፤ ወካዩም ሥልጣንን ሊሰጥ ወይም ሊነሣ የሚችለው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው (ሮሜ 13፡1፥4)።

## 2. ፖለቲካ ምንድን ነው?

ማንኛውም ኅብረተሰብ ለህልውናው መንግሥት እንደሚያስፈልገው ሁሉ፥ መንግሥትም ሕዝቡን በተገቢው መንገድ ለምምራት እንዲችል ደግሞ ጥበብ ያስፈልገዋል። ይህም ጥበብ ወይም ሳይንስ ፖለቲካ ተብሎ ይታወቃል። መንግሥት ከሌላ ኅብረተሰብ ውልቅልቁ

እንደሚወጣ ሁሉ፥ ያለ ፖለቲካም መንግሥት አይኖርም። ይህ የሚያሳየን በኅብረተሰብ፥ በመንግሥትና በፖለቲካ መካከል ያለውን ሊነጣጠል የማይቻል ግንኙነትና ትስስር ነው። የፖለቲካን መተኪያ የሌለው አስፈላጊነት በቅጡ ለመገንዘብ የፖለቲካን ምንነት በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።

"Politics" (ፖለቲካ) የሚለው ቃል የተወሰደው "Politikos" (ፖለቲኮስ) ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙ "Citizen" (ዜጋ) ማለት ነው። ፖለቲካን በሁለት መንገድ መረዳት ይገባል። ይኸውም ሰፊ በሆነውና ጠባብ በሆነው ትርጉሙ ነው። ፖለቲካን ሰፊ በሆነ መልኩ ካየነው የሚሰጠን ትርጉም አንድ ኅብረተሰብ በአንድ ላይ እንዲኖር የሚያስችል ጥበብ እንደሆነ ነው። ይህ አብሮ የመኖር ጥበብ የሚያስገኘው ጥቅም ሰው ብቻውን እና በግሉ ሊያሳካው የማይችለውን ነገር ያስገኝለታል። እነርሱም የፍትሕ፥ የመብት መከበር፥ ለሁሉም የሚሆን በጎ ነገር መገኘት፤ ውስጣዊ ሰላም (Internal harmony) መፍጠር፥ እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን ከሚነካ ክፉ ነገርና ጥቃት ከለላ ማግኘት ናቸው። እነዚህ ደግሞ እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረው የሰው ዘር ሁሉ ፍላጎቶች ናቸው። ሌላው የፖለቲካ ጥቅም ደግሞ ኅብረተሰቡ ውሳኔዎቹን ሁሉ እንዲወስንበት የሚያግዘው መሣሪያ መሆኑ ነው።

ፖለቲካን ከእነዚህ ጥቅሞቹ አኳያ ስናየው ቤተ ክርስቲያንም ሆነች እያንዳንዱ ክርስቲያን ከዚህ ኅብረተሰብን አስተሳስሮ በአንድነት እንዲያኖር ከሚታወቀው ጥበብ ውጭ መሆን ፈጽሞ አይችሉም። ኅብረተሰቡ እነዚህን ፍላጎቶቹን ሁሉ እንዲያሳካለትና እንዲያስከብርለት ሥልጣንና (Authority) ኀላፊነት (Responsibility) እንዲሁም ኃይል የመጠቀምን መብት (access to power) ሰጥቶ ያቋቋመውን የመንግሥትን ሚና እዚህ ላይ እናገኛለን። ይህ ደግሞ ፖለቲካን ጠባብ በሆነው መልኩ ወደ ማየት ይወስደናል።

ፖለቲካን ጠባብ በሆነው መልኩ ስንመለከተው የሚሰጠን ትርጉም ደግሞ አንድን ኅብረተሰብ ለመምራት ወይም ለማስተዳደር የሚያስችል ጥበብ ወይም ሳይንስ እንደሆነ ነው። ይህም የሚሆነው

ፖለቲካዊ ሥልጣንን በመያዝ የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና እና ማኅበራዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላትና ለመምራት በሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። የዚህም እንቅስቃሴ ዋነኛ ተዋናይ መንግሥት (Government) ነው። በዚህ የፖለቲካ ማለትም ሥልጣንን ይዞ በመምራት እንቅስቃሴ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በቀጥታ ተሳታፊ መሆን አይገባትም። ምክንያቱም ተልዕኮዋም ሆነ አቋሟ ይህንን አይፈቅድላትም። ይሁን እንጂ ክርስቲያን በግሉ በዚህ የፖለቲካ ሥልጣን ውስጥ ሊሳተፍ የሚችልበት ብዙ መድረኮች ያሉ ሲሆን፥ ያንንም በሌላ ክፍል በዝርዝር እናየዋለን።

## 3. የመንግሥት አመጣጥና አስፈላጊነት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር

የሰው ልጅ ከፈጣሪው ያታደለው አብሮ የመኖር ፍላጎት አለው። ሊቃውንቱም ይህንን የሚገልጹት «ሰው ማኅበራዊ ፍጡር» (social being) ነው በማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም የሚያረጋግጥልን ሰው ከሰው ጋር አብሮ እንዲኖር ከፈጣሪው የታቀደለት መሆኑን ነው። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም»፤ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት»፤ «በምድር ላይ ተዋለዱ እርቡባትም» (ዘፍጥ. 2፥18፤ 1፥28፤ 9፥7) የሚሉትና ሌሎችም አምላካዊ ትእዛዞች ይህንን በሚገባ ይመሰክራሉ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አብሮ ለመኖር እንዲችል አካሄዱን የሚቆጣጠርና የሚመራው ወደ አንድ ግብም እንዲደርስ የሚያስችለው አንድ የሥልጣን አካል (መንግሥት) ያስፈልገዋል። ይህንን ደግሞ አስቀድሞ ያወቀ፤ ተቋሙንም ለሰው ልጅ እንዲሆን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። ይህ እውነት በቆላስይስ 1፥16 ላይ እንዲህ በሚል ተጠቅሷል፦

> የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና... ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤

ይህ ክፍል በግልጽ እንደሚነግረን ሥልጣን ሁሉ፤ በሰማይ ያሉትና የማይታዩት ብቻ ሳይሆን በምድር ያሉትና የሚታዩትም በክርስቶስና ለክርስቶስ እንደተፈጠሩ ነው። ይህንንም በማጠናከር ስለ ሥልጣንም

ሆነ ስለ ባለሥልጣን ያለን አመለካከት እንዴት ሊሆን እንደሚገባ የሚነግረንና ተዘውትሮ የሚጠቀሰው በሮሜ 13፥1–7 ላይ የምናገኘው ክፍል ነው። ይህ ክፍል በግልጽ የሚያስተምረን አንደኛ፤ ሥልጣንም ሆነ ተሿሚዎቹ ከእግዚአብሔር በመሆናቸው ባለሥልጣናት እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ተደርገው መቆጠር እንደሚገባቸው፤ ሁለተኛ፤ ባለሥልጣናትን ማክበርና ለእነርሱም መገዛት ተገቢና እግዚአብሔርን እንደ ማገልገል መቆጠር እንደሚገባው፤ ሦስተኛ፤ እነርሱን መቃወም መለኮታዊም ሆነ ምድራዊ ቅጣትን የሚያስከትል መሆኑን ነው።

የባለሥልጣናት ተልዕኮ ከእግዚአብሔር እንደሆነና ወደ ሥልጣንም የሚያመጣቸው የሥልጣን ሁሉ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር እንደሆነ 1ኛ ጴጥሮስ 2፥13–14 እና ትንቢተ ዳንኤል 4፥32 ያረጋግጡልናል። እነዚህና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚያስገነዝቡን እንደ ቤተሰብና እንደ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ መንግሥትንም ከባለጠግነቱ የተነሣ ለጥቅማችን እንዲሆን የሰጠን እግዚአብሔር መሆኑን እንጂ ዓለም ያወቃቸው ፈላስፋዎች (Hobbes, Locke, Rousseau) እንደሚከራከሩበት ቅድመ አያቶቻችን ከተገባቡት ማኅበራዊ ውል (Social contract) የተነሣ መንግሥት እንዳልተገኘ ነው።

እግዚአብሔር መንግሥትን ሲሰጠን ሁለት ተልዕኮዎች እንዲኖሩት አድርጎ ሲሆን ከእነዚህም ተልዕኮዎቹ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሁለት ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፦

## ሀ/ ክፉ አድራጎትን እንዲገታ

የሰው ልጅ በኃጢአት የወደቀ ፍጡር በመሆኑ ኃጢአተኛ ባሕርይው ወደ ወንጀል የሚነዳው፥ የልቡ አሳብና ምኞትም ክፉ መሆኑን የሚያውቅ እግዚአብሔር (ዘፍጥ. 6፥5) ይህንን የሰው ኃጢአተኛ ባሕሪ የሚቆጣጠርና የሚገድበው ባለሥልጣን ወይም መንግሥት ተሾመለት። ይህንንም ተልዕኮውን በተገቢው መንገድ እንዲወጣ ክፉ የሚያደርጉትን የሚቀጣበት ሥልጣን (ሰይፍ) አስታጠቀው (ሮሜ 13፥4፤ 1ኛ ጴጥ. 2፥14)።

## ለ/ ለሰው መልካም እንዲያደርግ

የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት የወደቀ ፍጡር ቢሆንም መልካም የሆነውን ሁሉ ማግኘት እንዲችል፣ ሕግና ሥርዓትም ተጠብቆለት በሕይወት እንዲኖር እንጂ ደሙ በከንቱ እንዳይፈስ ፈጣሪው አስቀድሞ አስቦለታል። እግዚአብሔር ለዚህ የሰጠው ምክንያትም በአምሳሌ የፈጠርኩት ክቡር ፍጥረቴ ነው የሚል ነው (ዘፍጥ.9፡6)። ከዚህ በመነሣት ይህንን ለሰው ልጅ ያለውን መልካም አሳብ የሚያስፈጽምለትና በቃሉ አገልጋዬ ብሎ የሚጠራውን ባለሥልጣን ወይም መንግሥትን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሰጠ (ሮሜ 13፡3፥ 1ኛ ጴጥ 2፡14)።

ከእነዚህ ሁለት ምክንያቶች የምንገነዘበው እግዚአብሔር በምድራዊ መንግሥት አማካይነት ሰው በውስጡ ካለው ኃጢአተኛ ባሕርይው የተነሣ እርስ በርሱ ተጠፋፍቶ እንዳያልቅ የሚከላከል፣ እንዲሁም ሕግና ሥርዓት ባለበት ሁኔታ በሰላም እንዲኖር የሚያስችለውን ተቋም እንዳበጀለት ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ምድር ፈጽሞ የተበላሸችና ብጥብጥ (chaos) የነገሠባት፣ የሰው ዘርም ፈጣሪው አስቀድሞ ወዳዘጋጀለት የሰላም ሕይወት መድረስ የማይችል፣ አሁን የደረሰበት የሥልጣኔና የእድገት ደረጃ ፈጽሞ የማይታሰብ፣ አሳዛኝ ፍጡር ሆኖ ይቀር ነበር።

## 4. የመንግሥታት ዐይነት ከእግዚአብሔር አሳብ አንጻር

እግዚአብሔር መንግሥትን የሰጠበት ሁለት ተጓዳኝ ምክንያቶች ከላይ እንደተመለከትነው ሲሆን፣ የሰው ልጆችም ከዚህ የእግዚአብሔር አሳብ ጋር የሚጣጣም ወይም የሚፃረር የመንግሥት ዐይነት ለመመሥረት ሲታገሉ ኖረዋል። ከእነዚህም ውስጥ ሦስቱን፣ ማለትም ሥልጣንን ሁሉ ጠቅልሎ የሚይዘውን የቶታሊቴርያን (Totalitarian) ሥርዓትን፣ የመንግሥት ሥርዓት አያስፈልግም ብሎ የሚከራከረውን አናርኪንና (Anarchy) በሕዝብ ምርጫ የመንግሥት ሥልጣን የሚያዝበትን የዲሞክራሲ ሥርዓትን (Democracy) እግዚአብሔር ሥልጣንን ከሰጠበት ሁለት አሳቦች ጋር በማስተያየት ቀጥሎ እንመለከታቸዋለን።

# ቶታሊቴርያን መንግሥት

ቶታሊቴርያን በመባል የሚታወቀው የመንግሥት ዐይነት ሕዝቡን በማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የማያሳትፍ፣ ለሕዝቡ ምንም ዐይነት የውሳኔ ድርሻ የማይሰጥ፣ ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን በብቸኝነት የሚያውቁና የሚወስኑ መሪዎች ያሉበት የመንግሥት ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሰው የፈጣሪው ሳይሆን የመንግሥት ሀብት ይሆናል። ይህ ዐይነት መንግሥት አስቀድመን ካነሣናቸው እግዚአብሔር መንግሥትን ለምን እንደሰጠን ከተጠቀሱት ሁለት ዋነኛ አሳቦች ውስጥ አንዱን ይኸውም ሰው የወደቀ ፍጡር በመሆኑ አካሄዱን የሚቆጣጠርና የሚገድብ የሥልጣን አካል ያስፈልገዋል የሚለውን ብቻ ይዞ ሌላኛውን የእግዚአብሔርን አሳብ የጣለ በመሆኑ መሠረታዊ በሆኑ የሕዝብ መብቶችና ተቋሞች ላይ ጽኑ ቁጥጥር ያደርጋል።

ይህ የአገዛዝ ዐይነት በንጉሥ በሚተዳደሩና (Absolute Monarchy) በአንድ ፓርቲ ሥርዓት በሚመሩ አገሮች ውስጥ የተለመደ ሲሆን፥ በተለይ በአፍሪካ ውስጥ በሰፊው ይታያል። የዚህ ሥርዓት ደጋፊዎች የሚሰጡት ምክንያት የአፍሪካ መንግሥታት በጎሳ የተከፋፈለ ሕዝብ ያላቸው በመሆኑና የብዙሀን ፓርቲ ሥርዓት ደግሞ ሕዝቡ በጎሳ እንዲደራጅ በር ስለሚከፍት የአገር አንድነት ይዳከማል፤ ከዚህ ይልቅ በአንድ ጠንካራ ፓርቲ ሥር መሆን ለአገር አንድነት የተሻለ አማራጭ ነው የሚል ነው። ይህ አባባል እውነትነት ያለው ቢሆንም አገዛዙ በሕዝቡ ላይ የሚያስከትለው አደጋ ግን ከሚነገርለት ጠቀሜታ ይልቅ በእጅጉ የከፋ ነው። በዚህ ዐይነት አገዛዝ ውስጥ መንግሥትም ሆነ ሕዝቡ የመሪዎቹ የግል ሀብት ተደርገው ስለሚቆጠሩ መሪዎቹ ለሕዝቡ ካሰቡለት የተለየ አቋም ይዞ መገኘት የሕዝብ ወይም የመንግሥት ጠላት ተደርጎ (State Enemy) ያስቆጥራል።

በቶታሊቴሪያን ሥርዓት ውስጥ የመሪዎቹ ሥልጣን ከሕግ በላይ ስለሚሆን ሥልጣንን በእጃቸው ለማቆየት ማንኛውንም ሕግ የማይፈቅደውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ። የሕዝቡ ልዩ ልዩ ተቋማት የኃይማኖትን ጨምሮ በቁጥጥራቸው ሥር ይወድቃሉ፤ የትምህርት፣ የፍትሕና የንግድ ሥርዓቶች ለእነርሱ በሚጠቅም መልኩ ይደራጃሉ። ይህንን ዐይነት ሥርዓት በአገራችን በንጉሠ ነገሥቱ በኋላም በከፋ

መልኩ በደርግ ሥርዓት አይተናል። እንዲህ ዐይነቱ ፍጹማዊ አምባገነን ሥርዓት ከሕዝብ ጋር ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ሥልጣንን ከሰጠበት መለኮታዊ አሳብም ጋር የተጋጨ በመሆኑ ይዋል ይደር እንጂ መውደቁ የማይቀር ነው።

## አናርኪ/መንግሥት አልባ

አናርኪ የሚለው ቃል የመጣው ከግሪክ ሲሆን መንግሥት አልባ ወይም ሥርዓት አልባ (without government / without rule) ማለት ነው። አናርኪዝም በዓለማችን ላይ ተቀባይነትን ያገኘ ሥርዓት ባይሆንም፥ ለዚህ ጽንሰ አሳብ የቆሙና ይህ ሥርዓት እንዲመሠረት ይታገሉለት የነበሩት ሰዎች የሚያምኑት አንድን ተቋም በሕዝብ ላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አድርጎ መሾም አግባብ ካለመሆኑም በላይ ኢ ግብረገባዊ (Immoral) እንደሆነ ነው። ለዚህ የሚሰጡት ምክንያትም ሰው በተፈጥሮው ራሱን በራሱ ማስተዳደር የሚችል፣ በጥልቀትም ማሰብ የሚችል ፍጡር (Rational being) በመሆኑ፥ ከላይ ሆኖ በሞግዚትነት የሚያስተዳድረው ሌላ አካልም ሆነ እንቅስቃሴውን የሚገድቡ ሕግጋት አያስፈልጉትም የሚል ነው።

የዚህ አሳብ አራማጆች በራሺያ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ በብዛት የነበሩ ሲሆን፥ የተማሪዎች ንቅናቄ በዓለም ላይ ገንኖ በነበረበት በ1960ዎቹ እና በ1970ዎቹ ይህ እንቅስቃሴ በእጅጉ ተስፋፍቶ ነበር። ይህንን ሥርዓት በኃይል ለማቋቋም ይንቀሳቀሱ በነበሩ ክፍሎች የተነሣ የብዙ ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል። ከእነዚህም ውስጥ የራሺያ ዛር፣ የኦስትሪያ ንግሥት እንዲሁም የአሜሪካና የፈረንሳይ ፕሬዚዳንቶች ይገኙበታል። የዚህ ሥርዓት ናፋቂዎች ዋነኛ ስሕተት የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት የወደቀ ፍጡር መሆኑን አለመገንዘባቸው ነው። እነዚህ ክፍሎች ቢሳካላቸው ኖሮ በምድር ላይ ታላቅ ምስቅልቅል ይፈጠር ነበር።

እንግዲህ በአንድ በኩል የቶታሊቴሪያን ሥርዓት የሰው ልጆችን መልካም ገጽታ የማያገናዝብና ጨለምተኛ (Pessimistic) አመለካከት ያለው በመሆኑ የሰውን ክቡር ፍጡርነት ከጽና ረግጦ ለመግዛት በመሞከሩ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የአናርኪዝም ደጋፊዎች ብሩሃውያን (Optimistic) በመሆናቸው የሰው ልጆችን መልካም ገጽታ ብቻ

በመቀበል ነገር ግን ሰው በኃጢአት ምክንያት የወደቀ ፍጡር መሆኑን ረስተው ለሰው ልጆች ያልተገደበ ነጻነት ሊሰጣቸው ይገባል በማለታቸው ሁለቱም ተሳስተዋል። የሁለቱም የስሕተት መነሻ በትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ (Biblical Doctrine) ላይ አለመመሥረታቸውና ስለ ሰው ልጆችም ያላቸው አመለካከት የተዛባ ነው፥ ውጤቱም የተሳሳተ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ እንዲዘፈቁ አድርጓቸዋል። የመጀመሪያው ፍጹም የሆነ አምባገነንነትን እንጂ ፍትሕንና መልካም አስተዳደርን የማያመጣ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ብጥብጥንና ሥርዓት አልበኝነትን እንጂ የተመቻቸ ማኅበራዊ ሥርዓትን አያመጣም። ቢሆንም ከአናርኪ ሥርዓት ይልቅ ቶታሊቴሪያን ይመረጣል፤ ምክንያቱም የቱንም ያህል ጨቋኝ ቢሆንም ሕግንና ሥርዓትን ማስከበር የሚችል ሥልጣን ያለው አካል አለ።

## ዲሞክራሲ

በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ መንግሥት ሥልጣን የሚይዘው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሚደረግ የሕዝብ ምርጫ ነው። ዲሞክራሲ መሠረታዊ የሆነውን የሰው ልጅ መብት የሚያስከብር ነው ከመባሉም በተጨማሪ ሰላምን፣ ፍትሕንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንደሆነ ይታመናል። ሕዝቡንም በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያሳትፋል። ከዚህም በላይ በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ያለው የአወሳሰን ሂደት፤ አንደኛ፣ በተለያዩ አሳቦች ላይ በቂ ክርክር ተደርጎ፤ ሁለተኛ፣ ለሕዝቡ የሚጠቅም መሆኑ በሚገባ ታይቶ፤ ሦስተኛ፣ በአብላጫ ድምፅ ተወስኖ ነው። ዲሞክራሲ የሰውን ደካማ ጎን ከግንዛቤ ያስገባ በመሆኑ ሥልጣን ወደ አንድ ወገን እንዳያዳላ የሚያደርግ፣ የሥልጣን ክፍፍል የነገሠበት ሥርዓት ነው። ከዚህ በመነሣት ዲሞክራሲ በሰው ልጅ ተጨባጭ እውነታ ላይ የተመረኮዘ ሥርዓት ነው ለማለት ይቻላል። ይህም ማለት ሰው የወደቀ ፍጡር ስለሆነ ሕግና ሥርዓት ተበጅቶለት መተዳደር የሚገባው፣ እንዲሁም ሰው ክቡር ፍጥረት ስለሆነ ሰብአዊ መብቱ ሊከበርለት እንደሚገባ ያምናል።

ሁለት ዐይነት የዲሞክራሲ ሥርዓቶች ያሉ ሲሆን፥ አንደኛው ሥርዓት የመጨረሻውን የሥልጣን ባለቤትነት (The Ultimate Authority) ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሲሆን፥ ሌላኛው ግን ይህንን

ባለቤትነት ለሕዝቡ የሚሰጥ ነው። ለክርስቲያኖች የመጀመሪያው የዲሞክራሲ ዐይነት የተመረጠ ነው፤ ምክንያቱም የሥልጣን ሁሉ ባለቤት የሆነውን፣ በሰው ልጆች መንግሥትም ላይ ለዘላለም የሚሠለጥነውን (ዳን.4፡32) ልዑል እግዚአብሔርን የበላይ የሚያደርግ በመሆኑ ነው። ስለ ዲሞክራሲ ይህን ማለት ቢቻልም ከሌሎቹ ሥርዓቶች ይልቅ የተሻለ ተመራጭ ያደርገው እንደሆን እንጂ ፍጹም የሆነ ሥርዓት አድርገን መቁጠር ግን አይገባም።

ቶታሊቴሪያን ጨቋኝ አገዛዙን በሕዝቡ ላይ በግድ ስለሚጭን፣ አናርኪ ደግሞ ሥልጣን አስፈላጊ እንዳልሆነ ስለሚቆጥር ሁለቱም ለሰው ልጅ አይበጁም። በተጨማሪም የሰው ልጅ አሁን ለደረሰበት የእድገት ደረጃ ፈጽሞ አይሠሩም። ስለዚህም ሦስተኛውን የመንግሥት ዐይነት እርሱም ዲሞክራሲን ከሌሎቹ ይልቅ የተሻለ ተመራጭ ያደርገዋል።

እንግዲህ ከላይ እንደ ተመለከትነው እግዚአብሔር አምላካችን የሰው ልጅ በሥርዓት እንዲኖር አስቦ ባለሥልጣንን ወይም መንግሥትን እንደ ሰጠን ካመንን፥ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ተቋም ጋር ሊኖራት የሚገባው ግንኙነት ምን መምሰል ይገባዋል? የሚለው ጥያቄ ተያይዞ መታየት አለበት፤ ይህንንም በሚቀጥለው ክፍል እናያለን።

## 5. የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ ከመንግሥት ጋር ያላት ግንኙነት የተለያየ መልክና ቅርጽ ሲይዝ ቆይቷል። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥታት ጋር ይህ ነው የሚባል ግንኙነት ያልነበራት ቢሆንም፥ መንግሥታት ግን በተለይም የሮም መንግሥት የፖለቲካ ሥርዓት አጀንዳ አድርጓታል። ይህም የፖለቲካ ዘመቻ የቤተ ክርስቲያን መሥራችና ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከውልደቱ ጀምሮ እስከ መስቀሉ ድረስ ለስደት ዳርጎታል። ምንም እንኳ ከምድራዊ ሥልጣን እራሱን ቢያርቅም፣ መንግሥቱም ከዚህ ዓለም እንዳልሆነች አስረግጦ ቢናገርም፥ በወቅቱ የነበሩት የፖለቲካ ኀይሎች ማለትም የሮም ገዢዎችና የአይሁድ ሸንጎ ግን እርሱ በሚለው መንገድ ሊረዱትና ሊቀበሉት ፈጽሞ አልቻሉም። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ፤ እርሱ እያቋቋመው ያለው አዲስ ሥርዓት ለዘመናት ተንሰራፍተው የቆዩትን ማኅበራዊ

ግንኙነቶች (social relations) በሙሉ የሚያፋልስ መሆኑ ስላሳሰባቸው ነበር።

ለቄሳር ግብር መክፈል ተገቢ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ የተጠየቀው ተንኮል የሞላበት ጥያቄ (ሉቃ. 20፡19–26)፣ እንዲሁም ጲላጦስ ሊፈታው ፈልጎ ሳለ አይሁድ ግን የቄሳርን ሥልጣን የሚቀናቀነውን መፍታት ተገቢ እንዳልሆነ ያስፈራሩበት (ዮሐ. 19፡12) እና ሌሎችንም ክሶች ስንመለከት ጌታን የፖለቲካ ሰለባ ለማድረግ የተወጠኑ ሤራዎች እንደነበሩ እንረዳለን።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 11፡48 ላይ እንደተገለጸው፥ የአይሁድ አለቆች ሸንጎ ሰብስበው የተጨነቁበትና የመወያያቸው ርእስ የሆነው ዋነኛ ጉዳይ የኢየሱስ ተከታይ ማፍራትና እንዲሁ ቢተዉት ደግሞ ሮማውያን መጥተው አገሩንም ሕዝቡንም ይወስዳሉ የሚል ነበር። በጊዜው ግን አገሩም ሆነ ሕዝቡ በሮም ሥር የነበረ ሲሆን፥ እነርሱን ያስፈራቸው የክርስቶስ ተከታይ ማፍራት ሮምን ቢያስቆጣ የሚወሰደው እርምጃ ያላቸውን ውሱን የፖለቲካ ሥልጣን የሚያሳጣ ሊሆን እንደሚችል በመጠራጠራቸው ነበር። አይሁድ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የሚያስችላቸው ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን እንዲሁም ከሽማግሌዎች ተውጣጥቶ የተዋቀረና የተወሰነ ሥልጣን ያለው የአይሁድ ሸንጎ (Sanhedrin) የሚባል ነበራቸው። ይህ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ ምክንያት ያልነበረው ስጋታቸው የሞት ፍርድ እንዲፈርዱበት አነሣሥቶአቸዋል።

ወደ መጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ በመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት ከመንግሥት ጋር ይህ ነው የሚባል ግንኙነት ሳትመሠርት፣ ተሳትፎዋ ማኅበራዊ በሆኑ ጉዳዮች (Social Action) ዙሪያ ብቻ ተወስኖ ቆይቷል። ወላጅ አልባ ልጆችን፣ መበለቶችንና ችግረኞችን መደገፍ፣ ሕመምተኞችን መጠየቅ፣ እስረኞችን መጎብኘት፣ ባሪያዎችን በገንዘብ እየገዙ ነፃ ማውጣትና እንግዶችን መቀበል ቤተ ክርስቲያን የምትታወቅበት አገልግሎቷ ነበረ። ይህ አገልግሎቷ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ቢሆንም፥ ያለፍላጎቷ የፖለቲካቸው አጀንዳ ባደረጓት ነገሥታት ምክንያት ግን ለልዩ ልዩ ጥቃት ተጋልጣለች።

የመጀመሪያው ችግር የተፈጠረው ክርስትና እና የአይሁድ እምነት አንድ አለመሆናቸው ሲደረስበት ነበር። አይሁዶች ከሌሎች በሮም

ግዛት ሥር ከሚኖሩ ልዩ ልዩ ሕዝቦች በተለየ የገዛ እምነታቸውን እንዲያራምዱ ሕጋዊ (religio licita or legal religion) ፈቃድ ተሰጥቷቸው ነበር። ክርስትናም የአይሁድ እምነት ተቀጽላ (sect) ተደርጎ ይወሰድ ስለነበረ የዚህ ሕጋዊ ከለላ ተጠቃሚ ሆኖ ቆይቷል። ሆኖም፣ በዚሁ አልዘለቀም፤ ክርስትና የተለየ መሆኑ ሲደረስበት ይህንን የሕግ ከለላ አጣ። ሁለተኛውና ዋነኛው ችግር የተፈጠረው «ክርስቶስ ወይስ ቄሳር» (<<Christ or Caesar>>) የሚለውና ማንን የበላይ ማድረግ እንደሚገባ የሚፈተሽበት ጥያቄ ሲመጣ ነበር። በዘመኑ በሮም አስተዳደር ሥር በነበሩ ግዛቶች ውስጥ የነበሩትን የተለያዩ ሕዝቦች የሚያስተሳስር ተድርጎ የታሰበው ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም (political ideology) የሮም ቄሳሮችን እንደ ጌታና አምላክ (dominus et deus/lord and god) አድርጎ መቀበል ነበር። ይህም የዜግነትና የታማኝነት መግለጫ ተደርጎ ይቆጠር ስለነበር አንድ በሮም ግዛት ሥር የሚኖር ዜጋ የመረጠውን የትኛውንም ዐይነት እምነት ለመከተል ፈቃድ ያገኝ የነበረው አስቀድሞ የቄሳሮችን አምላክነት ሲቀበል ብቻ ነበር። ይህ ማንን የበላይ እናድርግ የሚለው ጥያቄ ወደ ክርስቲያኖች ሲለንዘር ግን ጉዳዩ የሮምን ገዢዎች የሚያሳስብ ሆነ። ለክርስቲያኖች አምልኮና መታዘዝ ያለተቀናቃኝ በብቸኝነት የሚገባው ክርስቶስ በመሆኑ የጌትነቱንና የአምላክነቱን ስፍራ የሚሰጡት ለቄሳር ሳይሆን ለክርስቶስ መሆኑ ተደረሰበት። ይህም ክርስቲያኖች የሮም ዋነኛ ጠላት ተደርገው እንዲቆጠሩ ምክንያት ሆነ።

ሦስተኛው ችግር ደግሞ ክርስቲያኖች በሮም መንግሥት ላይ በድብቅ የሚያሤሩ ኃይሎች ተደርገው እንዲቆጠሩ ያደረገ ነበር። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱት፤ አንደኛ፣ ክርስቲያኖች በፍርሀትም ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ስብሰባቸውን በድብቅና በምሽት ያደርጉ ስለነበር፤ ሁለተኛ፣ በመካከላቸው የሚነሡትን ችግሮች ወደ ገዢዎች ሳይወስዱ ራሳቸው በራሳቸው ይፈቱት ስለነበር፤ ሦስተኛ፣ በአሕዛብ መቅደሶችና በጨዋታ ስፍራዎች ከሚደረጉት ዓለማዊ ዝግጅቶች ራሳቸውን ያገልሉ ስለነበር ነው። እነዚህና ሌሎችም ሁኔታዎች ሁሉ ተደማምረው የሮም ገዢዎች በክርስቲያኖች ላይ እንዲነሡና በክርስትናም ላይ ሕገ ወጥ እምነት (Religio ilicita/Illegal religion) የሚል ድንጋጌ እንዲያወጡ ምክንያት ሆነ።

ይህም እስከ ቆስጠንጢኖስ (Constantine) ዘመን ድረስ በዘለቀውና እስከ ዛሬም ድረስ ወደር ባልተገኘለት ከባድ መከራ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እንድታልፍ ምክንያት ሆነ። ይህ ሁሉ የሚያስገነዝበን ቤተ ክርስቲያን ወደ ፖለቲካው ባትጠጋም ነገሥታት ግን የፖለቲካ አጀንዳቸው እንዳደረጓት ነው።

ክርስትና ሕጋዊ ሃይማኖት እንዲሆን ደንብ ከወጣበት ከቆስጠንጢኖስ ዘመን (313 ዓ.ም) ጀምሮ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መቀራረብ የጀመሩበት ወቅት እንደነበረ ይታወቃል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመንግሥት ዘንድ ሥልጣን ያገኙበት፥ እንዲሁም ነገሥታት ለቤተ ክርስቲያን በሚያደርጉት አስተዋጽዖና ጥበቃ ሰበብ በመንፈሳዊና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት የጀመሩበት ሁኔታ ተከሰተ። ከዚህም በላይ ይህ ወቅት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ለበላይነት ያደርጉት የነበረው ረጅምና አስከፊ ትግል የተጀመረበት፤ በሁለቱ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነትም በተለያየ መንገድ እንዲተረጎምና እንዲተገበር ሰፊ በር የከፈተ ነበር ለማለት ይቻላል። በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች የተነሡ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋና የሆኑትን ሦስቱን እንደሚከተለው እናያለን።

## የካቶሊኮች አመለካከት

የካቶሊክ ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያንንና የመንግሥትን የተነጣጠለ ሚና ቢቀበሉም በአብዛኛው ግን ቤተ ክርስቲያንን የበላይ መንግሥት ደግሞ የበታች አድርገው ይመለከታሉ። ለዚህም ልዩ ልዩ ምክንያቶችን የሚሰጡ ሲሆን በቀዳሚነት፤ መንግሥት ጊዜያዊና ምድራዊ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ግን ዘላለማዊና ሰማያዊ በመሆኗ ነው በማለት ይከራከራሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል 16፡19 ላይ ለጴጥሮስ የተሰጠው የሥልጣን ቁልፍ ቤተ ክርስቲያን መንግሥትን የመቆጣጠር ሥልጣን እንዲኖራት የሚያደርግ ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ በተለይ የመካከለኛው ዘመን ሊቃውንት፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ሲናገሩ በሉቃስ 22፡38 ላይ እንደተጠቀሱት ሁለት ሰይፎች ይመስሉታል። አንዱ ሰይፍ የቤተ ክርስቲያን የራሷ የሥልጣን ምንጭ ሲሆን፥ ሌላኛው ግን ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት የምታስታጥቀው ሰይፍ ነው ይሉ ነበር።

በተጨማሪም ይህንኑ የቤተ ክርስቲያንን የበላይነት ለማረጋገጥ በመፈለግ አንዳንድ ሐሰተኛ መረጃዎች (Forged Documents) እስከ ማቅረብ ደርሰዋል። ከእነዚህም ሐሰተኛ መረጃዎች ውስጥ አንደኛው ከቆስጠንጢኖስ ተሰጠን የሚሉት (Donation of Constantine) ሲሆን፥ የሚደነግገውም የሮም ካቶሊክ ጳጳስ በአውሮፓ በሚገኙ ግዛቶች ሁሉ የበላይ ሆኖ እንዲቆጠር፥ መሳፍንቱም ሆኑ ነገሥታቱ ታማኝነታቸው ለጳጳሱ እንዲሰጡ የሚል ነው። ሌላው ተገኘ የተባለው የሐሰት መረጃ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቷ መሥራቾችና የመጀመሪያዎቹ ጳጳሳት (Bishops) ከሆኑት ከሐዋርያት እንደሆነና የሚደነግገውም የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን (Universal Church) ላይ ያላቸውን ፍጹም የሆነ የበላይነትና (Absolute Supremacy) ቤተ ክርስቲያንም ከመንግሥት ተጽዕኖ በፍጹም ነፃ የሆነች፣ አገልጋዮቿም በየትኛውም የመንግሥት አካልም ሆነ ፍርድ ቤት መጠየቅ የማይገባቸው እንደሆኑ ነው።

ይህ የቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊውንም ሆነ የፖለቲካውን የበላይነት የመፈለግ አካሄድ በአንዳንድ ደካማ ነገሥታት ተቀባይነት ቢያገኝም አንዳንድ ጠንካራ ነገሥታት ግን ሲቃወሙት ኖረዋል። በተለይ ከ11ኛው እስከ 14ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአውሮፓን መንፈሳዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሕይወት መቆጣጠር ችለው ነበር። ሆኖም ይህ መንግሥታትን በበላይነት የመቆጣጠር አካሄድ ብዙ ችግር ያስከተለና ከባድ ተቃውሞ የገጠመው በመሆኑ፣ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንሥቶ በተለይም ደግሞ ከተሐድሶው ዘመን በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፖለቲካው ላይ የነበራቸውን ተጽዕኖ እያጡ ሄደዋል።

## የአናባፕቲስቶች አመለካከት

የአናባፕቲስት እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ዘመን እየተስፋፋ የመጣ ሲሆን፥ በወቅቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የታላቁ ተሐድሶው አራማጆች የነበሩት እነ ሉተርና ሌሎቹም ይከተሉት የነበረውን ሕፃናትን የማጥመቅ ሥርዓት በጽኑ ይቃወሙ የነበሩ ናቸው። አናባፕቲስቶች በቤተክርስቲያንና በመንግሥት መካከል

ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የያዙት አቋም ከተሐድሶው መሪዎች አቋም ጋር በፍጹም የሚቃረን ነበር። የእነርሱ አቋም የሚያተኩረው፣ በሁለቱ ተቋማት ፍጹም መለያየትና በመካከላቸውም ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊፈጠር አይገባም በሚለው ዙሪያ ነበር። አናባፕቲስቶች መንግሥት አስፈላጊ እንደሆነ ቢቀበሉም፣ ሰይጣን ግን ለራሱ አሳብ ማራመጃ ተቆጣጥሮታል ብለው ስለሚያምኑ እውነተኛ አማኞች ከዚህ ሥርዓት መራቅ አለባቸው በማለት ያስተምሩ ነበር። በምርጫ መሳተፍ፣ በመንግሥት ሥልጣን ላይ መቀመጥ፣ በወታደርነት ማገልገል ወይም በየትኛውም የመንግሥት ተግባር ላይ መሳተፍ ለክርስቲያኖች ተገቢ አይደለም የሚል አቋም ነበራቸው። በሌላ አነጋገር የመንግሥት ሥርዓት ዓለማዊ በመሆኑ ለዓለማውያን ብቻ መተው እንዳለበት በብርቱ ይከራከሩ ነበር።

ይህ አቋም የአናባፕቲስት መንፈሳዊ ልጆች እንደሆኑ በሚታወቁት በተወሰኑ ሜኖናይቶችና አሚሽ በሚባሉት ዘንድ አሁንም ድረስ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፥ የይሖዋ ምስክሮችም የዚህ አቋም ዋነኛ ደጋፊዎች ናቸው። በዚህ አናባፕቲስቶች በያዙት አቋም ምክንያት ከካቶሊክም ሆነ ከተሐድሶው መሪዎች በኩል ከፍተኛ የሆነ መከራና ስደት ደርሶባቸዋል።

## የሉተራንና የካልቪኒስቶች አመለካከት

የሁለቱ አቋም በአብዛኛው ቢቀራረብም አንዳንድ መለያየቶች ግን ነበሯቸው። እንደ ሉተርም ሆነ ካልቪን እምነት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ለተለያየ ተልዕኮ ከእግዚአብሔር የተሰጡ፣ የሁለቱም የሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር እንጂ የካቶሊክ ሊቃውንት እንደሚሉት መንግሥት ሥልጣኑን የሚያገኘው በቤተ ክርስቲያን በኩል ነው የሚለውን አይቀበሉም። ስለዚህም የሁለቱም የበላይ እግዚአብሔር እንጂ አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ ሊሆን እንደማይገባ፣ እንዲሁም አማኞች የመንግሥትም ሆነ የቤተ ክርስቲያን አካል በመሆናቸው ለሁለቱም ኀላፊነት አለባቸው በማለት ሉተርና ካልቪን ያምናሉ። ሆኖም በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትብብር እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋን ለማሳካት የመንግሥትን ሥልጣን በመጠቀም ጉዳይ ላይ ይለያያሉ። እንደ ሉተር እምነት ቤተ ክርስቲያን የምስራቹን ወንጌል ስታውጅ፣ መንግሥት ደግሞ ሕግን ያውጃል። በመሆኑም ሁለቱም የየራሳቸው የሆነ

የአገልግሎት ድርሻ ስላላቸው አንዱ በአንዱ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ተገቢ አይደለም። አማኞችም የክርስትናን መርሆዎች በመንግሥታዊ ሥራዎች ላይ በአግባቡና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ማዋል ቢችሉም የያዙትን የመንግሥት ሥልጣን መጠቀሚያ በማድረግ ክርስትናን ለማስፋፋት መሞከር አይገባቸውም።

ካልቪን በተቃራኒው መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን መደገፍና መጠበቅ እንዲሁም ክርስትናን ለማስፋፋት ተልዕኮዋን ማገዝ እንደሚገባው ይቀበላል። በሁለቱ ተቋማት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትብብር ከማንም በላይ ጽኑ አቋም ቢኖረውም መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ግን ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ተጽዕኖ ነፃ እንደሆነች ያምናል። ከዚህ አቋሙ በመነሣት መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ሥልጣን አጣምሮ በመያዝ ካልቪን የጄኔቫ ከተማን (City state) ያስተዳድር ነበር።

## 6. በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖሩ የሚችሉ ግንኙነቶች

የመጽሐፍ ቅዱስንና የታሪክን ማስረጃ አጣቅሰን ከላይ እንደተመለከትነው የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ልዩ ልዩ መልክ ሲይዝ ቆይቷል። አንድ ጊዜ መንግሥት አሳዳጅ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ተሳዳጅ በመሆን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ቁጥጥር ውስጥ ገብታ የነገሥታት አገልጋይ በመሆን፣ በኋላ ላይ ደግሞ የመንግሥትን ሥልጣን በእጇ አስገብታ የነገሥታት ሿሚና ሻሪ በመሆን ብዙ ዘመን አልፍዋል።

ከታላቁ የተሐድሶ ዘመን በኋላ የነገሠው አመለካከት ደግሞ ሁለቱ ተቋማት የተለያዩና አንዱ በሌላው ላይ የበላይ ሊሆን እንደማይገባው ቢገልጽም፥ ሲሠራበት የነበረው ግን ነገሥታቱ የተቀበሉትን እምነት የሕዝቡ እምነት የማድረግ አካሄድ ነበር። በ18ኛው ክፍለ ዘመን የተከሰቱት የአሜሪካና የፈረንሳይ አብዮቶች ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖር በሚገባው ግንኙነት ላይ ታላቅ ለውጥ አምጥተዋል። ይህም አዲስ የግንኙነት አሳብ በሁለቱ መካከል ፍጹም መነጣጠል (Separation) እንዳለ የሚሰብክና መንግሥት የትኛውንም ዐይነት እምነት መደገፍ የለበትም የሚል ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ አሁን ባለንበት ዓለም በተለይም በዲሞክራሲ ሥርዐት በሚመሩ

አገሮች ያለው ሁኔታ የተለያየ ገጽታ አለው። በአሜሪካ ያለው የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ፍጹም በሆነ መለያየት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች ያለው ሁኔታ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት የተቀራረበ ግንኙነት የጠበቀ ነው። እንደ እንግሊዝ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድንና በመሳሰሉት አገሮች ደግሞ መንግሥት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እስከ መሾም ድረስ የሚሄድ ትስስር አላቸው። ሆኖም አንዱ ሌላውን የመጫንና አንዱ በአንዱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት አካሄድ እንዳይኖር ጥንቃቄ ያደርጋሉ።

ከእነዚህ የተለያዩ ገጽታዎች አንጻር በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉትን ግንኙነቶች በሚቀጥሉት ሦስት መንገዶች ከነጥቅማቸውና ጉዳታቸው ማስቀመጥ ይቻላል።

## ሀ/ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት ሲቆጣጠር

ይህ ሁኔታ ሲከሰት ቤተ ክርስቲያን መንግሥት ሕዝቡን ከሚያስተዳድርበት መገልገያዎቹ (State Machineries) እንደ አንዱ ሆና መቆጠር ትጀምራለች። በዚህ ወቅት ለቤተ ክርስቲያን የሚያስገኝላት ጥቅም ተግባሯን ለማከናወን የሚስፈልጋትን የመንግሥት ትብብር በቀላሉ ታገኛለች፤ እንዲሁም ከየትኛውም አቅጣጫ ጥቃት እንዳይሰነዘርባት አስተማማኝ ጥበቃ ያስገኝላታል። ነገር ግን በዚህ ረገድ ከሚገኘው ጥቅም ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያስከተለው ጉዳት ያመዝናል። ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ መደገፍ ስትጀምር ይህንኑ ላለማጣት የእግዚአብሔር ሳይሆን የመንግሥት አፍና ጆሮ ሆና ማገልገል ትጀምራለች፤ ለደህንነትዋም የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን የክርስቶስን ፊት ሳይሆን የገዥዎችን ደጅ መጥናትና በእነርሱም ላይ መደገፍ ትጀምራለች፤ በሃይማኖት አንድነት ሰበብ ነገሥታትንና ገዢዎችን በማግባባት እምነቷን በኀይል ለማስፋፋት የተለየ እምነት በሚያራምዱ ላይ ትዘምታለች። ይህ ሁኔታ በአገራችን ብዙ ጊዜ የተከሰተ ሲሆን፥ በዚሁ ሰበብ ካቶሊኮች፣ ፕሮቴስታንቶች፣ የእስልምና ተከታዮች ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል፤ እንዲሁም በወንጊላውያን አማኞች ላይ የተካሄዱ እና አሁንም እየደረሱ ያሉ ጥቃቶች ሁሉ የዚሁ ዘመቻ አካል ናቸው።

ሌላው የሚያስከትለው ጉዳት ደግሞ ነገሥታት ለቤተ ክርስቲያን በሚያደርጉት ድጋፍ ሰበብ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ እጃቸውን እንዲያስገቡ መንገድ የሚከፍት መሆኑ ነው። በአገራችን ነገሥታት ለቤተ ክርስቲያን በሚያደርጉት አስተዋጽኦ መለኪያነት እንደ መንፈሳዊ መሪ ተደርገው በመቆጠራቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ ጥፋት አምጥተዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ተደማምረው ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሰማያዊ ተልዕኮና ጸጋዋን በማስጣል፣ ፋይዳ በሌለው ሃይማኖታዊ ሥርዓት የተሞላች ምድራዊ የሃይማኖት ድርጅት ብቻ ትሆናለች።

## ለ/ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት የበላይ ስትሆን

ይህ ሁኔታ የሚያስገኘው ጥቅም መንግሥት በክርስትና መርሆዎች ላይ እንዲመሠረት ከማድረጉም በላይ የሚያወጣቸው ሕጎችም የክርስትናን እሴቶች (values) እንዲያንጸባርቁ ያደርጋል፣ ክርስትና የግል ወይም የተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ጉዳይ ይሆናል፣ ቤተ ክርስቲያንም ተልዕኮዋን ያለገደብ እንድታከናውን ያስችላታል። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ ስትሠለጥን ከላይ ካየነውም በእጅጉ የከፋ ሁኔታ ይፈጠራል። በእግዚአብሔርና በሰው መካከለኛ ለመሆን ሥልጣን የተሰጠውን ክርስቶስን በመጋፋት ሥልጣኑን የራሷ ማድረግ ትጀምራለች። በዚህም በክርስቶስ በኩል ብቻ የሚገለጠውን ለሰው ሁሉ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ታጣለች። ይህም በጸጋው ብቻ የሚሆነውን ሰውን የማዳን ተልዕኮ ታጣለች፣ ይህንንም ለማካካስ ምድራዊና ሥጋዊ ስልትን በመቀየስ በወንጌል ኃይልና በፍቅር ሳይሆን፣ ሠይፍን በማንሣትና ከክርስትና ሥነ-ምግባር ውጭ በሆነ መንገድ የተለየ እምነትን የሚከተሉትን ለማሳመን ትነሣሣለች።

በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በገለጠው በቃሉ ሥልጣን ሥር መሆን ሲገባት፣ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ በመሆን በራሷ ሥልጣን መቆም ትጀምራለች። ይህ ሁኔታ በመካከለኛው ዘመን ላይ በመከሰቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሥታትንና ገዥዎችን ያስገብሩና ያሰግዱ ነበር። ይህንን መቀበል ባቃታቸው ላይ ደግሞ ብዙ ችግር ያደርሱባቸው ነበር። ለምሳሌም ግሪጎሪ 7ኛ (Gregory VII) የተባለው የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ ያላትን የበላይነት

በማስረገጥና እርሱም እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪነቱ ከነገሥታትና ከመሳፍንት በላይ መሆኑን፣ ደግሞም ሕግ የማውጣትም ሆነ የዳኝነት ሥልጣን (Legislative and Judicial Power) የእርሱ ብቻ እንደሆነ በድፍረት ያወጀ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበረ። ይህንን ሥልጣኑን መጋፋት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይጥል ነበር። የጳጳሱን ሥልጣን በመጋፋቱ ችግር ውስጥ ገብቶ የነበረው ሔንሪ 4ኛ (Henry IV) የተባለው ንጉሥ የዚህን ጳጳስ ይቅርታ ለማግኘት ወደሚኖርበት ስፍራ በመጓዝ ከግቢው ውጭ በበረዶና በቅዝቃዜ ውስጥ በባዶ እግሩ ሦስት ቀን በመቆም ደጅ ለመጥናት ተገድዶ ነበረ።

ፍሬዴሪክ የተባለው ንጉሥ ከሌላኛው የዚሁ ዘመን ጳጳስ ይቅርታን ለመቀበል በጳጳሱ ፊት ወድቆ እግሩን መሳሙ አልበቃ ብሎ የጳጳሱን ፈረስ ልጓም ይዞ እየጎተተ በሕዝብ ሁሉ ፊት በመሄድ የበታችነቱን ማረጋገጥ ነበረበት። ከዚህም በላይ ብዙ እልቂት ያስከተሉ የመስቀል ጦርነቶችን (Crusades) በማወጅ፥ እንዲሁም ሌሎችን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ ክፉ ጠባሳ ጥለው ያለፉ ድርጊቶችን በመፈጸም የሚጠቀሱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተነሡት እንዲህ ባለ ቤተ ክርስቲያን ተገቢ ቦታዋን የለቀቀችበት ሁኔታ ሲፈጠር ነበረ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ከሰጣት ተልዕኮ ውጭ መሆንዋን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ከሰጣት ሥልጣን በላይ ለመሆን በመጓጓቷ ሊገለጽ በማይቻል ታላቅ ውድቀት ውስጥ እንደገባች ነው።

### ሐ/ በመከባበርና መተጋገዝ ላይ የተመሠረተ ነገር ግን የተነጣጠለ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት

ይሄኛው ዓይነት ግንኙነት ከላይ ካየናቸው አንዱ የሌላው የበላይ ከሚሆንበት ሁኔታ የተሻለ ነው። ምክንያቱም በሁለቱ ተቋማት (Institutions) መካከል ጤናማና ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሁም በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ ነው። ይህንን በበለጠ ለመገንዘብ ሁለቱ ተቋማት ለሰው ልጆች የሚሰጡትን የአገልግሎት ድርሻ ጠቅለል ባለ መልኩ መዳሰስ ጠቃሚ ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ድርሻ እርሱም ዋነኛ ተልዕኮዋ የሆነው ሰውን ሁሉ በወንጌል መድረስ (Evangelism) ነው። ይህንንም የምታከናውነው በሦስት ዋና ዋና መመሪያዎች ላይ ተመሥረታ ነው። እነዚህም «እምነት»፣ «ተስፋ»፣ «ፍቅር» ናቸው። በእነዚህ መሠረትነት ነፍስን የማዳን፣ የአማኞችንም መንፈሳዊ ፍላጎት ማሟላትና ሰው በክርስቶስ ሁለንተናዊ ነጻነት እንዲያገኝ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሮቿ ሲሆኑ፥ በተጨማሪም የእግዚአብሔርን በጎ አሳብ፣ ምሕረቱን፣ ፍርዱንና ጽድቁን ለሰው ሁሉ ማወጅ ኀላፊነቷ ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ተያያዥነት ላላቸው ሁለት ነገሮች ይጠቅማል። <u>አንደኛው</u>፣ ሰው ከፈጣሪው ጋር ያለውን አምዳዊ (vertically) ግንኙነት በዕርቅ እንዲያስተካክል ሲረዳው፣ <u>ሁለተኛው</u> ደግሞ፥ ሰው ከሰው ጋር ያለውን አግድማዊ (horizontally) ግንኙነቱን እንዲያስተካክልና በኅብረተሰቡም ውስጥ ድርሻውን ጤናማ በሆነ መንገድ እንዲወጣ ይረዳዋል።

የመንግሥትን የሥራ ድርሻ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው፣ መልካም ወይም አዎንታዊ በሆኑት ሕግጋቶቹ የዜጎቹን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟሉ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን መቅረጽ፣ ሰላም፣ እኩልነትና ፍትሕ የሰፈነበት፣ የዜጎችም መብት የተከበረበት ሥርዓት መመሥረትን፣ አስገዳጅ ወይም አሉታዊ በሆኑት ሕግጋቶቹ ደግሞ ደካማው በኀያሉ እንዳይጠቃ መከላከልን፣ በዜጎቹ አካላዊ፣ አእምሮአዊና፥ ቁሳዊ ደህንነት እንዲሁም ተቋማቱ ላይ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጉዳት ሊያደርሱ የሚነሡትን በመቅጣት ሕግና ሥርዓትን ማስከበርን ያጠቃልላል።

ሁለቱ ተቋማት ለሰው ዘር የሚሰጡት ጠቀሜታ ጠቅለል ባለ መልኩ ይህንን ሲመስል፣ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ለሰው ልጅ የሚሰጡት ግልጋሎት ተወራራሽነት ያለውና የአንዱ አገልግሎት ለሌላው አስፈላጊ መሆኑን ነው። ይህንንም በመጠኑ ለማብራራት፤ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን የመስበክ ዋነኛ ተልዕኮዋን ለማከናወን ሰላምና የተረጋጋ ሁኔታ እንደሚያስፈልጋት እሙን ነው። ይህ ባልተረጋገጠበትና ምስቅልቅልነት (chaos) በሰፈነበት ሁኔታ ውስጥ ሰዎችን በወንጌል መድረስ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። ለምሳሌ በመጀመሪያው ዘመን ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ወደ ሌሎች

ሰፍራዎች ሊደርስ እንዲችል የሮም መንግሥት ያሰፈነው ሰላም (Pax Romana/ The Roman Peace) አስፈላጊ ነበረ። አለበለዚያ ግን ከአገር አገር ይደረግ የነበረው የሐዋርያት ጉዞ በተለይም የጳውሎስ ረጅም ጉዞ አዳጋች ይሆን ነበር። አሁን ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ በምሳሌነት ብናነሣ፣ ለወንጌል ሥራ ከሶማሊያ ይልቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ይሻላል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ ሕግንና ሥርዓትን የሚያስከብር መንግሥት ሲኖር፥ በሶማሊያ ግን የተደራጀ መንግሥት ባለመኖሩ ጠመንጃ የታጠቀ ሁሉ በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የሚያደርግባት ምድር ስለሆነች ወንጌልን ለመስበክ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል።

በተጨማሪም ከመንግሥት ሚናዎች አንዱ በሕዝቡም ሆነ በሕዝቡ ተቋማት ላይ ጥቃት እንዳይደርስ መከላከል እንደሆነ አስቀድመን አይተናል። በዚህም ረገድ ቤተ ክርስቲያን የሕዝብ ተቋም በመሆኗ የመንግሥትን ጥበቃ ታገኛለች። ይህም ደግሞ ጠቀሜታ እንጂ አንዳች ጉዳት የለውም። ጉዳት ግን የሚመጣው ቤተ ክርስቲያን ራስ ሆኖ በሚጠብቃት መሥራቿ ላይ ያላትን መተማመን ጥላ ከመንግሥት በሚገኘው ድጋፍ ላይ መተማመን ስትጀምር ነው።

እንደዚሁም፣ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ኅብረተሰብ ውስጥ ያላት የሥራ ድርሻ መንግሥት በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊያከናውነው ባቀደው ተግባሩ ሁሉ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ አለብን። መንግሥት ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፣ ፍትሕ እንዳይጓደል፣ የተመጣጠነ እድገት እንዲያመጡለት የሚያወጣቸውን ሕጎቹን፣ ፖሊሲዎቹንና ፕሮግራሞቹን የሚያስፈጽመው በሰዎች ነው። ለዚህም ዓላማው ግብ መምታት መልካም አዕምሮ ያላቸው፣ ዝና እና የግል ጥቅማቸውን ሳያስቀድሙ ለሥራ የሚተጉ፣ ሳያዳሉ ሰውን ሁሉ በእኩል የሚያገለግሉ ሰዎች እንደሚያስፈልጉት አጠያያቂ አይሆንም። እነዚህ ደግሞ አዕምሮአቸው የታደሰ፣ መጽሐፍ ቅዱስም የምድር ጨው የሚላቸው፣ የቤተ ክርስቲያን ፍሬዎች ናቸው። ለአንድ አገር ጥሩ መሪ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ጥሩ ተመሪም አስፈላጊ በመሆኑ ምድራዊ መንግሥት የዚህ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተቋዳሽ ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የሚታየው የአገልግሎት መደጋገፍ ከዚህ ያለፈ ቢሆንም፣ መንግሥት ለሌሎች ተቋማት

የሚያደርገውን ድጋፍና ጥበቃ ለቤተ ክርስቲያንም ከማድረግ ውጭ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ከመግባት፣ ቤተ ክርስቲያንንም በተጽዕኖው ሥር ከማድረግ መቆጠብ አለበት። ቤተ ክርስቲያንም መንግሥትን እንደ እግዚአብሔር ዓይንና ጆሮ ሆና ከመምከርና ከማሳሰብ በስተቀር በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ መግባት፤ በመንግሥትም ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ከመሞከር መቆጠብ አለባት። እዚህ ላይ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ መንግሥት በመንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አይገባም ቢባልም፥ ቤተ ክርስቲያን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከሰጣት ሥልጣን ውጭ በመሄድ እና ሕግንም በጣሰ መንገድ እምነቷን በሌሎች ላይ በጉልበት ለመጫን ብትነሣ ይህን አካሄድ ለማስቆም መንግሥት ጣልቃ የመግባት ሕጋዊ ሥልጣን አለው።

ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ከሥራ ድርሻቸው የተነሣ ተደጋጋፊነት አላቸው ቢባልም፥ አንደኛ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ተቋማት ከመሠረተበት ዓላማ መለያየት የተነሣ፤ ሁለተኛ፣ አገልግሎታቸው ከሚያተኩርበት የሥራ ድርሻና ክልል መለያየት የተነሣ የተቋም ልዩነት እንዳላቸው ይታወቃል። ይህም የተቋም ልዩነት በተቻለ መጠን ተጠብቆ መኖር ይገባዋል። ይህንን በሚገባ ለመረዳት የሚያተኩሩበትን የሥራ ድርሻና ክልል በንጽጽር መልክ የሚያሳዩትን የሚከተሉት አምስት ነጥቦች እንመልከት።

ሀ. መንግሥት በዋነኛነት የሚያተኩረው በሰው አእምሮአዊ፣ አካላዊና ቁሳዊ ሕይወቱ ላይ ሲሆን፥ የሚቆጣጠረውም የተገለጠና ውጪያዊ የሆነውን የሰው አካሄድ ነው፤ ይህንንም በሕግ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ኃይልን በመጠቀም ያከናውናል። የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ትኩረት ግን ውስጣዊ የሆነው የሰው የነፍሱ ጉዳይ ሲሆን፥ መሣሪያዋም ቃሉና መንፈሱ ብቻ ናቸው።

ለ. መንግሥት ዜጎቹን በሙሉ እንደ አካሉ የመቆጣጠርና ለሁሉ እኩል ኀላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ዜጋ የሆነውን ሁሉ እንዲሁም የኅብረተሰቡን ተቋማት በሙሉ በማስተዳደር ሥልጣኑ ሥር ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያን የምታቅፈው ግን ፈቃደኛ የሆኑትንና በአብዛኛው በኅብረተሰቡ ውስጥ ካሉት የተወሰኑትን ክፍሎች ብቻ ነው።

ሐ. መንግሥት የተሾመው በዚህ በኃጢአት ምክንያት በተበላሸው ዓለም ውስጥ ላለው የሰው ልጅ ሕግና ሥርዓት አበጅቶ በሰላም

እንዲኖር ለማስቻል ነው። ይህ ግን ሰውን ከኃጢአቱ የሚያላቅቅ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ግን እግዚአብሔር በሰጣት የደኅንነት ወንጌልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰውን ከኃጢአቱና ከክፉ ሥራው የማላቀቅ አገልግሎት አላት።

መ. መንግሥት የውጭ ፖሊሲ ቀርፆ ከሌሎች መንግሥታት ጋር ግንኙነት ቢያደርግም በአብዛኛው ግን የሚመለከተው በራሱ የግዛት ክልል ውስጥ ያለውን ሲሆን፤ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮና እንቅስቃሴ ግን በአንድ ግዛት ውስጥ የማይወሰን ዓለም አቀፋዊነት ባሕርይ ያለው ነው።

ሠ. መንግሥት ተለዋዋጭ ከሆነው የውስጥና የውጭ ሁኔታ ጋር የራሱን አቋም እያዛመደ የሚጓዝ፤ የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችም ጊዜያዊና ዘለቄታዊ ሁኔታዎችን እያገናዘቡ የሚሄዱ ሲሆኑ፤ ቤተ ክርስቲያን ግን የተመሠረተችው ዘለዓለማዊ በሆነ እውነት ላይ በመሆኑ የቆመችለት ዓላማና የምታስተላልፈው መልእክት ከተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታ ጋር የሚለዋወጥ አይደለም።

ሁለቱ ተቋማት ያላቸው የሥራ ድርሻ በአንድ በኩል ተደጋጋፊነት ያለው፤ አንዱ ለአንዱ ጠቃሚ እንደሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አገልግሎታቸው የሚያተኩርበት የሥራ ድርሻና አድማስ የተለያየ ነው ቢባልም ተልዕኳቸው የሚያተኩረው ግን የሰው ልጅ ከኃጢአተኛ ባሕርይውና ራስ ወዳድነቱ የተነሣ እርስ በርሱ ሳይጠፋፋ ዓለም ሳይፈጠር ፈጣሪው ወዳዘጋጀለት የደኅንነት ግብ እንዲደርስ ማስቻል ነው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ፤ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ መንግሥትን የእግዚአብሔር አገልጋይ በማለት የሚጠራቸው። ይህን ከላይ የተመለከትነውን የሥራ ድርሻ በተመለከተ ማርቲን ሉተር ሲገልጸው ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ትሰብካለች፤ መንግሥት ደግሞ ሕግን ይሰብካል በሚል ሲሆን፤ የካልቪን አገላለጽ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ነፍስን ስትመራ፤ መንግሥት ደግሞ ሥጋን ይመራል የሚል ነው።

ይህ እንዲህ ከሆነ፤ ማንኛውም ክርስቲያን የእነዚህ የሁለቱ ተቋማት አባል መሆኑን መረዳትና እግዚአብሔር የወሰነላቸውን ተልዕኮ ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውስጥ የገዛ ድርሻውን ማበርከት አይጠበቅበትምን? የእግዚአብሔርስ ፈቃድ አይደለምን? (ዕብ. 13፡17፤

ሮሜ 13፥6-7፤ 1ኛ ጢሞ. 2፥1-4፤ ቲቶ 3፥1፤ 1ኛ ጴጥ. 2፥15፤ ማቴ. 22፥21)

## 7. ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት የምታበረክተው አገልግሎት

ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት የምታበረክተው በመንግሥትና በሃይማኖት መካከል ያለው ግንኙነት ትክክለኛ አካሄድን የተከተለና ግልጽ ሲሆን ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠውን አገልግሎት በዝርዝር ከማየታችን በፊት ይህንን በመጠኑ መዳሰስ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት ፖሊሲን የሚከተል መንግሥት እንደሚሻለን ለመለየት ይጠቅማል።

ታሪክ እንደሚዘክረን በአንድ አገር (Nation) አጠቃላይ የሕይወት አቅጣጫ ውስጥ ሃይማኖት የሚይዘው ስፍራ የተለያየ ትርጉምና ክብደት ሲሰጠው ኖሯል። ቀጥሎ የተቀመጡት አራት ነጥቦች ይህንኑ ያስረዳሉ።

*ሀ/ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥና የመተዳደሪያ ሕጋቸው ሰጪ ተደርጎ የሚቆጠርበት ሥርዓት።* ይህ ዓይነት ሥርዓት «አምላክ-ገዝ» (Theocratic State) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፥ በሕዝቡ ተቀባይነት ያለው አንድ ሃይማኖት ብቻ ያለ ሲሆን፥ ይህም ኃይማኖት የኅብረተሰቡ መሠረት ተደርጎ የሚቆጠር ነው። ይህ ዓይነት የመንግሥት ሥርዓት በቀደምት እስራኤል ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፥ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ምሪት በቀጥታ መርጦ በሚሾማቸውና እንደ ወኪሉ በሚቆጥራቸው አስተዳዳሪዎች ይተዳደሩ ነበር።

*ለ/ አገር አቀፍ የሆነ መንግሥታዊ ተቀባይነትና ድጋፍ ያለው አንድ ቤተ ክርስቲያን (State Church) ያለበት ሥርዓት።* በዚህ ዓይነት ሥርዓት ውስጥ ከዋናው አገር አቀፍ እምነት የሚለዩ ሌሎች እምነቶች ሊኖሩ ቢችሉም፥ በመንግሥት በኩል ግን ይህ ነው የሚባል ተቀባይነት የሌላቸውና በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው። ለዚህም እንደ ጀርመንና ስዊድንን የመሳሰሉ የአውሮፓ አገሮችን ምሳሌ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል።

*ሐ/ ፀረ ሃይማኖት አቋም ያለው የመንግሥት ሥርዓት።* ለሃይማኖት ምንም ዓይነት እውቅናና ክበሬታ የማይሰጥ፥ በተቃራኒው

ግን የፀረ ሃይማኖትና የክህደት (Atheism ) ፕሮፓጋንዳ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝበት የኮሚኒዝም ሥርዓትን የሚወክል ነው።

*መ/ ሃይማኖትን በተመለከተ ገለልተኛ አቋም ያለው፣ ከየትኛውም ሃይማኖት ጋር የማይወግን፣ የመንግሥት ሃይማኖት የሚባል የሌለበት ወይም ዓለመኛ መንግሥት (Secular State) ሥርዓት።* በአሜሪካና በሕንድ ያሉ መንግሥታት ለዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ተጠቃሽ ምሳሌ ናቸው። እነዚህ መንግሥታት ያሏቸው የየራሳቸው ሕገ መንግሥት የዜጎቻቸውን የእምነት ነጻነትና ሃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን (Religious values) ያከብራሉ። በሃይማኖት-አልባ መንግሥት አመራር ላይ የሚቀመጡት የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሃይማኖቶች ተከታይ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ። ነገር ግን በኅብረተሰቡ መካከል ጤናማ የሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖር ለማስቻል ለየትኛውም ሃይማኖት አያደሉም።

አሁን በአገራችን ያለው መንግሥት ዓለመኛ (ሃይማኖት-አልባ) ሲሆን፥ ይህም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ከአንድ በላይ ሃይማኖቶች ለሚገኙባቸው አገሮች ከላይ ካየናቸው የመንግሥትና የሃይማኖት ግንኙነቶች ሁሉ የተሻለ ተመራጭ ያደርገዋል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚደረግ ለአንድ ሃይማኖት የማድላት አካሄድ ውጥረትንና አለመተማመንን በኅብረተሰቡ መካከል ስለሚፈጥር ጤናማ ማኅበራዊ ሕይወት እንዳይኖር እንቅፋት ይሆናል።

አስቀድመን እንዳየነው በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ቤተ ክርስቲያንን የመንግሥት አንዱ አካል (department) የሚያደርግ ወይም መንግሥትን በቤተ ክርስቲያን ተጽዕኖ ሥር የሚያደርግ መሆን የለበትም። የሁለቱም ሥልጣን በውክልና ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው (delegated authority) እንጂ የሥልጣናቸው ምንጭ ራሳቸው ባለመሆናቸው ተጠያቂነት አለባቸው። ተጠያቂነታቸውም የሥልጣናቸው ምንጭ ለሆነው ለወከላቸው ለእግዚአብሔር እንጂ አንዱ ለአንዱ ሊሆን አይችልም። ይህ ማለት ግን፣ አንዱ ሌላውን ሊገባበት ካለው ስሕተትም ሆነ እያደረሰ ካለው ጥፋት የመመለስ ኀላፊነት የለበትም ማለትም አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ኀላፊነት ሁለቱንም የሚመለከት ቢሆንም ኀላፊነታቸውን የሚወጡበት መንገድ ግን በእጅጉ ይለያያል። ለምሳሌ፣

ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ኃይል ሳይሆን የእምነት ነጻነትን በመጋፋትና የሌሎችን መብት በመጨፍለቅ እምነቷን ለማስፋፋት ብትነሣ፣ መንግሥት በክፉ የሚሄዱትን ለመቅጣት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ይህንን ለመግታት ሕግ የሚፈቅድለትን ሁሉ ወይም እንደ ሮሜ 13፡4 አባባል ሰይፍን እስከ መጠቀም የሚሄድ እርምጃ የመውሰድ መብት አለው።

እንደዚሁም፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓይንና ጆሮ ሆና ማገልገል ይገባታል ሲባል፣ ይህ አገልግሎት መንግሥት ጉዳትን የሚያመጣ ከሕዝቡም ሆነ ከእግዚአብሔር አሳብ ጋር የሚጋጭ አካሄድን ሲከተል መክሮና አስጠንቅቆ የመመለስ ኀላፊነትንም ይጨምራል። ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን ይህንን ኀላፊነቷን በፍቅርና በትሕትና መሥዋዕትነትንም በመክፈል እንጂ በኀይል ወይም በሰይፍ የማከናወን መብት አልተሰጣትም።

የቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባር ከሆነው የምስራቹን ቃል ከመስበክ እንዲሁም እያንዳንዱ አማኝ በሚኖርበት በክፉው በተያዘው ዓለም ውስጥ ብርሃን ሊሆን የሚያስችለውን አስፈላጊ መንፈሳዊ ትጥቅ ከማስታጠቅ ባሻገር በኀብረተሰቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት አሳብ ሰርፆ እንዲገባ የማድረግ አገልግሎት አላት። ለዚህም ምክንያቱ ክርስቶስ በሁሉም ላይ ሥልጣን ያለው ጌታ እንጂ ጌትነቱ በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ ብቻ የተገደበ ቀሪው የኀብረተሰቡ ሕይወት ግን ከዚህ መለኮታዊ ገዢነት የተነጠለ ባለመሆኑ ነው። የፖለቲካና የሥነ መለኮት ሰው የነበሩት አብርሃም ኩፐር (Abraham Kuyper) ይህንን ሁኔታ እንዲህ በማለት ገልጸውታል "There is not a single inch of which Chirst the Lord does not claim as His own" (ጌታ ክርስቶስ የእኔ ነው የማይለው አንድም ስንዝር ስፍራ የለም)። ይህ አገላለጽ እውነትነት ያለውና «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» (ማቴ. 28፡18) ከሚለው የክርስቶስ ቃል ጋር ይስማማል። ከዚህም በመነሣት የትኛውም የኀብረተሰቡ ሕይወት ፖለቲካንም ጨምሮ ከክርስቶስ ገዢነትና የበላይነት ውጭ ሊሆን አይችልም ለማለት እንደፍራለን።

በየትኛውም የሥልጣን ቦታ ላይ የተቀመጠ ባለሥልጣን ለክርስቶስ ጌትነት መገዛት እንደሚገባው ማስተማር፣ ማሳሰብና ማስጠንቀቅ ከማንም በላይ የሚመለከተው ቤተ ክርስቲያንን ነው። ማንኛውም ምድራዊ መንግሥት ትክክለኛ ፍትሕና መልካም አስተዳደር ሊመሠርት እንደሚገባው፣ ለሥልጣን ማራዘሚያና ለግል ጥቅም ሳይሆን ለሕዝቡ የሚበጅ ተገቢ የሆነ ፖሊሲን ሊቀርጽ እንደሚገባው፣ የሥልጣኑን ገደብ በሚገባ የሚገነዘብና ከዚያ ውጭ የማይሄድ ሊሆን እንደሚገባው፥ ይህም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና በፊቱም መልካም መሆኑን መግለጽና ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ሌላው ተልዕኮዋ ሊሆን ይገባል። ይህንን ካልኩ በኋላ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም እንዴት አድርጋ መንግሥትንና ኅብረተሰቡን ልታገለግል እንደምትችል እንደሚከተለው እናያለን።

## ሀ/ በጸሎት ማገልገል

ቤተ ክርስቲያን ስላለችበት ኅብረተሰብም ሆነ ስለ መንግሥት ተግታ የመጸለይ፣ ምእመናኗም በግልም ሆነ በኅብረት ስለ መንግሥታቸውና ስለ አገራቸው እንዲጸልዩ የማስተማርና የማነሣሣት ኀላፊነት አለባት (1ኛ ጢሞ. 2፡1-2)። የጸሎት አገልግሎት በሥልጣን ላይ ባሉት የመሪዎች ዓይነትና ሁኔታ የሚወሰን አይደለም። ለሃይማኖት በአጠቃላይ ወይም ለክርስትና በተለይ በጎ አመለካከት የሌላቸው፣ ወይም ሌላ እምነትን የሚከተሉ፣ ወይም ከተለያዩ የክርስትና ክፍሎች ውስጥ አንዱን ደግፈው ሌላውን የሚያገልሉ ቢሆኑም እንኳን ለእነዚህ መሪዎች መጸለይ የማይስተጓጎል የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሆን ይገባዋል። በሌላ አነጋገር መሪዎቻችን የመምረጥ ዕድሉ ባለበት አገር የምርጫ ድምፃችንን እንነፍጋቸው እንደሆነ እንጂ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ግን ስለ እነርሱ መጸለይንና ማሳየት የሚገባንን ከበሬታ መንፈግ ግን አንችልም። እዚህም ላይ ሊታሰብበት የሚገባው ትልቁ ጉዳይ በጸሎት ሰበብ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ለፖለቲካ ወገናዊነት ማንጸባረቂያና ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ነው።

በቅንነትና በእውነት ለመሪዎች የሚደረግ ጸሎት የሚኖረው ጠቀሜታ ብዙ ሲሆን፥ ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

1. የጸሎት ኀይል መሪዎች የተሾሙበትን ዓላማ በመተላለፍ የማይገባ አቅጣጫ እንዲከተሉ በአእምሮአቸው ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርገው ከክፉው አሠራር እንዲላቀቁና በአእምሮአቸው ለእግዚአብሔር መልካም አሳብ ተገዢ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል (2ኛ ቆሮ.10፡3−6)።

2. እግዚአብሔር ፊት በሚቀርብ ጸሎትና ምልጃ መሪዎች ለአገሪቱ በአጠቃላይ የሚበጅ መልካም ነገር እንዲያከናውኑ ጠቃሚ የሆኑ ፖሊሲዎችን እንዲቀርጹ፥ መለወጥ የሚገባቸውን እንዲለውጡ ማድረግ ይቻላል። ምክንያቱም የመሪዎች ልብ ክፉና የማያምን ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር እጅ በመሆኑና ተስማምተን በእግዚአብሔር ፊት ያቀረብነው ልመናም በከንቱ የማይቀርና ዋጋ ያለው በመሆኑ ነው (ምሳ. 21፡1፤ ማቴ. 18፡19−20)።

3. መሪዎቻችንን በጸሎት ስናግዝ፣ ሰላምንና ሥርዓትን የማስፈን ኀላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይረዳቸዋል። በውጤቱም፣ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሰዎችንም ሁሉ ወደ ደኅንነትና እውነትንም ወደ ማወቅ የሚያመጣውን ወንጌል የመስበክ ተልዕኮዋን በሰላም እንድታከናውን ለቤተ ክርስቲያን ሰፊ በር ይከፈትላታል (1ኛ ጢሞ. 2፡3−4)።

ለባለ ሥልጣናት፣ ለሕዝቡና ለአገር በትጋት የሚደረግ ጸሎት እጅግ ኃይል ያለውና የሚሠራ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ይመሰክራል። በተቃራኒው ግን ክርስቲያኖች በግልም ሆነ በኅብረት ስላሉበት ኅብረተሰብ፣ ስለ መሪዎቻቸው እና ስለ አገራቸው ባይጸልዩ፣ ከሰላም ይልቅ ዓመፅ ይሠለጥናል፤ ከፍትሕ ይልቅ ጭቆና ይበዛል፤ እግዚአብሔርን ከመፍራት ይልቅ ክህደትና ግድየለሽነት ይነግሣል። ይህ ደግሞ በአጠቃላይ በሕዝቡ ወይም በአገሪቷ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲገለጽ ምክንያት ይሆናል።

## ለ/ የእርሾነት (Leaven) አገልግሎት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በማቴዎስ ወንጌል ላይ (13፡33) ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲያስተምር «መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች» በማለት ነው። ተልዕኮዋን በተገቢው መንገድ

የምትወጣ፣ ለክርስቶስ ጌትነት ሙሉ ለሙሉ የምትገዛና ብርሃኗ ሁልጊዜ የበራ፣ ተከታዮችዋንም አስፈላጊ በሆነው መንፈሳዊ ትጥቅ የምታስታጥቅ ቤተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰርፆ እንዲገባ የማድረግ ኃይል ይኖራታል። ይህም ሕዝቡ በሁሉም መስክ ማለትም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ሕይወቱ ላይ ታላቅ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችለው የእርሾነት አገልግሎት ነው። እንዲህ ያለው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሁለት መንገድ ይከናወናል፣ ጨው እና ብርሃን በመሆን (ማቴ. 5፡13-16)። ክርስቲያኖች ከሌላው የሚለዩት በዚሁ ጨውና ብርሃን በመሆን ባሕርያቸው እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስገነዝባል። ይህ ልዩ የሆነ ባሕርይ ከዓለም ጋር በመደባለቅ ጣእሙን እንዳያጣ ከዓለም መለየት አስፈላጊ እንደሆነም ቃሉ አጥብቆ ያስጠነቅቃል። ነገር ግን ይህ ከዓለም የመለየት ጉዳይ ከኅብረተሰቡ በመነጠል የራስን ገለልተኛ ሕይወት መምራት፣ ወይም በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚሆነውን ከቶ ነገር እንዳላዩ መሆን፤ ወይም አያገባንም በሚል መንፈስ በርን መዝጋት ማለት አይደለም። ይህንን የምታደርግ ቤተ ክርስቲያን ውጤት ያለው ሥራ መሥራት ካለመቻሏም በላይ ባለችበትም ኅብረተሰብ ውስጥ ይህ ነው የሚባል ለውጥ ማምጣት ይሳናታል። ቤተ ክርስቲያን ጨውና ብርሃን የመሆን አገልግሎቷን በአግባቡ ለመወጣት እንድትችል፤ የኅብረተሰቡ ጤናማ ባህሉና የታሪኩ፣ የማግኘቱና የማጣቱ፣ የከፍታውና የውድቀቱ፣ የደስታውና የኀዘኑ አካል መሆንዋን በማሳየት በኅብረተሰቡ ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ዘልቃ መግባት መቻል አለባት። በዚህ ጊዜ ነው በኅብረተሰቡ መካከል ብርሃን የምትሆነው፤ ጨው በመሆንም ማኅበራዊ ዝቅጠት (social decay) እንዳይፈጠር የማድረግ ሥራ የምትሠራው። አልያ አለሁ ማለቷ ስም ብቻ ይሆንባታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ላለችበት ኅብረተሰብ ብርሃንና ጨው መሆን የማትችል «ቤተ ክርስቲያን» ሕያውነቷም ያጠራጥራል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ ዘልቃ መግባት አለባት ቢባልም፣ ያላትን ክርስቲያናዊ እሴቶቿን (Christian values) የሚጎዳና መንፈሳዊ አገልግሎቷን የሚያስጥል ዓይነት መቀላቀል ከዓለም ጋር ማድረግ አይገባትም። ይሄ ማባከን ነው። የእርሾነት ባሕርይውንና ይዘቱን የያዘ እርሾ የገባበትን ሊጥ ይለውጣል

እንጂ ራሱ እንደማይለወጥ ሁሉ፣ እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያን ማንነቷንና ያላትን በመጠበቅ የለውጥ ኃይል መሆን እንጂ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው ችግር እርሷ ራሷ መወሰድ አይገባትም። ኅብረተሰቡ ዋጋ የሚሰጠው ነገር ከእግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ ጋር የሚጋጭ ከሆነ ነገር ሁሉ ካልሸሸችና ከመካከልዋም ካላስወገደችው እንኳንስ ተደማጭነት ያለው ምስክር መሆን ቀርቶ በውጭ ያለው ችግር ወደ ውስጧ እየሰረገ በመግባት ሊያፈርሳት የሚንጣት አሳዛኝ ስፍራ ትሆናለች። ይህ ሁኔታ ማለትም በውጭ የሚታዩ ጊዜያዊ ችግሮች በአገራችን ባሉ አንዳንድ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሰርገው በመግባት ምእመናንን እስከ መበተን እየደረሱ እንደሆነ እያየን ነው።

በአንድ በኩል ወደ ኅብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ጨው መሆንን በሌላ በኩል ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ ካለ እድፍ ራስን በመጠበቅ ጤናማና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ያከናወነች ቤተ ክርስቲያን «በዓለም ውስጥ የመሆኗን» እና «ከዓለም ያለመሆኗን» መልእክት የተረዳች፣ ተልዕኮዋንም በሙላት መወጣት የምትችል ትሆናለች።

## ሐ/ የመንግሥት ኀሊና ሆኖ ማገልገል

ይህ አገልግሎት አስቀድመን ካየናቸው ከሁለቱ ይለያል። ለዚህም ምክንያቱ፤ አንደኛ፣ ይህ አገልግሎት በጥንቃቄ የሚከናወን፣ ወቅትም መምረጥ የሚያሻው በመሆኑ ነው፤ ማለትም ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ኅብረተሰብና መንግሥት አጠቃላይ ሁኔታ ወይም ዐውድ (context) አስቀድማ ማወቅና መገምገም የሚኖርባት ዓይነት አገልግሎት ነው። ሁለተኛ፣ በዚህ ዐይነት አገልግሎት ተቀባይነትን ለማግኘት አስቀድሞ የራስን ቤት ማስተካከል ግድ የሚሆንበት በመሆኑ ነው፤ የዘር ወይም የጎሳ ልዩነት የሚንጸባረቅባት፣ ባለውና በሌለው መካከል ልዩነት የምታደርግ፣ መልካም ስም የሌላቸው መሪዎች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ከበሬታና ተደማጭነትን ማግኘት አይቻላትም። ይህ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን የማይመች ሁኔታ ውስጥ ሊከትና በጥርጣሬ እንድትታይም ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄና ዝግጅት ሊደረግበት የሚገባ ነው። ይህንን አገልግሎት በብቃት ለመወጣት በትጋት መጸለይና ጊዜውን መዋጀት

ችል የሚባል ጉዳይ አይደለም። ይህ ዓይነቱ አገልግሎት የመምከር፥ የማስተማርና የማስጠንቀቅ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ሕዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን የሚላቸው፤ የእግዚአብሔርን በጎነት ለማወጅ የተመረጠ ትውልድ ያላት፤ ቤተ ክርስቲያን ናት። በተጨማሪም እግዚአብሔር ለሕዝቡም ሆነ ለምድሪቱ አሁን ያለውንም ሆነ የወደፊት አሳቡን የሚገልጽበትን የትንቢት መንፈስ የሰጣት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። ስለዚህም በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚከሰትን ክፉና እግዚአብሔርን የሚያሳዝን አካሄድን መጠቆም፤ ይህም ሁኔታ አድጎ ወደ ፊት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት አስቀድሞ በማየት መሪዎችንም ሆነ ሕዝብን ማስጠንቀቅ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ነው።

የኅብረተሰቡ አካል የሆኑ ነገር ግን ተገቢውን ትኩረት የተነፈጉ ድሆች፤ ጩኸታቸው ሰሚ ያጣና እየተበደሉ ያሉ አናሳ ወገኖች ትኩረት እንዲያገኙ ለተገቢው አካል ማሳሰብ፤ ሕዝቡን ማኅበራዊ ችግር ውስጥ የሚከቱ፤ ግፈኛ ለሆነ አሠራርም በር የሚከፍቱ ውሳኔዎችንና ፖሊሲዎችን መጠቆምና እንዲሻሻሉ ወይም እንዲለወጡ ለመሪዎች አቤት ማለት እንደ አገልግሎት መታየት ያለበት ነው። ይህም የሚሆነው በተቃውሞና በማሳጣት መንገድ ሳይሆን ክርስቲያናዊ በሆነ ትሕትና አክብሮት መደረግ የሚገባው አገልግሎት ነው። ከዚህም ጎን ለጎን ብሔራዊ ጠቀሜታ ያላቸው፤ የዜግነትና የሰብአዊ መብትን አያያዝ የተመለከቱ፤ የሥራ ሥነ ምግባርን (work ethics) ለማሻሻል የሚበጁ፤ የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ መቻቻልን ጠቀሜታ የሚያስገነዝቡና የአካባቢን ጥበቃ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለምእመኗ በማስተማር በአገር እድገት ላይ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ የምታደርግ ቤተ ክርስቲያን ላለችበት አገርና ኅብረተሰብ የምትሰጠው አገልግሎት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም።

አሁን በአገራችን ባሉት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አቅምና አቋም አንጻር ሲታሰብ ይህ እንደ መንግሥት ጎሊና ሆና የማገልገል ጉዳይ የማይጨበጥ ህልም ሆኖ ሊታይ ይችል ይሆናል። ትክክልም ነው። ነገር ግን ይህንን አገልግሎት ከግብ ለማድረስ

በተናጠል መንቀሳቀስ ባይቻልም አንድ ኅብረት በማቋቋምና በዚያ ጥላ ሥር በመሰባሰብ ይህንን አገልግሎት ዳር ማድረስ ይቻላል።

ለዚህም አገልግሎት የሚጠቅሙ ሦስት መንገዶች አሉ። <u>አንደኛው፣</u> የአገሪቱን ፖሊሲ ለሚያወጡና ለሚያስፈጽሙ፣ በልዩ ልዩ የአመራር ቦታ ላይ ለተቀመጡ ለሚኒስትሮች፣ ለፓርላማ ተመራጮች፣ ለኮሚሽነሮች፣ ለሥራ አስኪያጆችና ተደማጭነት ላላቸው ግለሰቦች የሚጠቅሙ ሴሚናሮችንና ውይይቶችን በማዘጋጀትና በልዩ ልዩ የሙያ መስክ ብዙ ልምድ ያካበቱ ታዋቂ ክርስቲያን የፖለቲካ ሰዎችን ከተለያዩ አገራት በመጋበዝ ትምህርት እንዲሰጡ፣ ልምዳቸውንም እንዲያካፍሉ በማድረግ ነው። ይህ ለሁለት ነገር ይጠቅማል፤ አንደኛው፣ መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ስልቶች ላይ ጠቃሚ ድርሻ የሚያበረክት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአገራችን የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሩቅ ተመልካች የመሆንን ባህል አስቀርቶ ጤናማ የሆነ ድርሻ ወደ ማበርከት ያመጣቸዋል፤ ይህም በተራው ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን በበጎ ዓይን ከማይመለከቱ ወገኖች፣ እስከ አሁን ሲሰነዘር የነበረውን ክስ ያስቀራል።

<u>ሁለተኛው</u> መንገድ በተለያዩ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አባል የሆኑ በተለያየ የኀላፊነት ቦታ ላይ የተሾሙ፤ በልዩ ልዩ የሙያ መስክ ጥሩ እውቀትና ልምድ ያላቸውን አማኞች በማስተባበርና መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ስልቶች ላይ ጠቃሚና ገንቢ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ ማኅበራትን (pressure groups) እንዲያቋቁሙ በመርዳት ነው። እነዚህም ማኅበራት በተቻለ መጠን መንግሥት በበጎ ዓይን የሚመለከታቸው፥ አፍራሽና ተቺ ሳይሆን ገንቢ የሆነ ሚና መጫወት የሚችሉ መሆን አለባቸው። የእነዚህ ማኅበራት አባላትም ባላቸውም እውቀትና ልምድ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እየታገዙ በልዩ ልዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥናቶችን በማካሄድና በሰነድ የተደገፉ አሳቦችን (proposals) በማቅረብ መንግሥትን ማገዝ ይችላሉ። ይህ ከላይ እንዳየነው ለአገር እንዲጠቅሙ መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ስልቶች ላይ ጠቃሚ የሆነ ድርሻ ማበርከት የሚያስችል መንገድ ነው።

ሦስተኛው መንገድ ስሚ ያጡ የኀብረተሰቡን ጉዳዮች፣ እየተጎዱ ያሉ የአናሳ ወገኖችንና (minorities) የድሆችን ጩኸት፣ እንዲሁም በአማኞች ላይ በእምነታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ጥቃት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና በአመራር ላይ ላሉ ባለሥልጣናት በግንባር ቀርቦ በማስረዳት ወይም በደብዳቤ በማስታወቅ ነው። «አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፥ ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ» (ምሳ. 31፡8) የሚለው የቃሉ ትእዛዝ አሁንም ሆነ ወደ ፊት የሚሠራ ነው። ይህም በምድሪቷ ላይ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ግፈኛ አሠራር እየበዛ እንዳይሄድ ለመከላከል ይጠቅማል።

## መ/ በመታዘዝና ባለመታዘዝ ማገልገል

መታዘዝን በተመለከተ ክርስቲያኖች ከመንግሥት ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ሐዋርያው ጳውሎስ ሮሜ 13፡1–7 ላይ ካስገነዘበው የተሻለ ክፍል የለም። ክርስትናም ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ባሉት ዘመናት በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ሁልጊዜ የሚጠቀሰው ይህ ክፍል ነው። ይህንን ክፍል ክርስቲያኖች ብቻም ሳይሆኑ ሥልጣናቸውና ያሉበት ሁኔታ ተጠብቆ (status quo) እንዲቀጥል የሚፈልጉ አምባገነን ገዢዎችም ሳይቀሩ መዝዘው ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት የፈራረሰው የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ሥርዓት ሰይጣናዊ አገዛዙን በአፍሪካውያን ላይ ለመጫን በሚያመች መልኩ ይህንን የሮሜን ክፍል ሲጠቀምበት ነበር።

በሮሜ ላይ የተመለከተውን ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ኀላፊነትን ሰጥቶ እግዚአብሔር የሾመውን ባለ ሥልጣን ወይም መንግሥትን መታዘዝና ማክበር በግልም ሆነ በኀብረት የሚደረግ የክርስቲያን ሁሉ ግዴታ መሆኑን 1ኛ ጴጥሮስ 2፡13–17፣ ቲቶ 3፡1 ላይ ያሉት ክፍሎችም ያረጋግጡልናል። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ፣ ጳውሎስና ጴጥሮስ ለምን መታዘዝ እንደሚገባ ሲጽፉ፣ አንደኛ ሥልጣን ሁሉ የሚገኘው ከእግዚአብሔር በመሆኑና ባለሥልጣናቱም እርሱን የሚወክሉ በመሆናቸው እግዚአብሔርን ከማክበር የተነሣ (ሮሜ 13፡1፣ 1ኛ ጴጥ. 2፡14)፤ ሁለተኛ፣ ከተግባራቸውም አኳያ ለመልካም ነገር የእኛ አገልጋይ እንዲሆኑልንና ክፉውን ነገር እርሱም የኃጢአት ውጤት የሆነውን ወንጀልን እንዲገቱልን የተሾሙ በመሆናቸው (ሮሜ

13፡4፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡14)፤ ሦስተኛ፤ መልካም ኀሊና እንዲኖረንና እግዚአብሔርን ለማገልገል ከመፈለግ የተነሣ ነው (ሮሜ 13፡5-6፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡13)። ስለዚህም የአማኝ መታዘዝ ባለሥልጣን የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚያስፈጽም አገልጋዩ አድርጎ ከመቁጠር የተነሣና ስለ ጌታ ብሎ በፈቃደኝነት እንጂ ቅጣት በመፍራት ብቻ መሆን እንደሌለበት፥ በተጨማሪም እግዚአብሔር በመልካምነቱ ለመሠረተው ሥርዓት መታዘዝ ምስክርነትን የሚያጠናክር መሆኑን በመገንዘብ እንደሆነ እነዚህ ክፍሎች አስረግጠው ይገልጻሉ።

እዚህ ላይ የሚነሣው የብዙዎች ጥያቄ በተገቢው መንገድ ወደ ሥልጣን የመጣውን፤ ሥልጣኑንም በአግባቡ የሚጠቀመውን መንግሥትና በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን ላይ የወጣውን፤ ሕዝቡንም ረግጦና አስጨንቆ የሚገዛውን አምባገነን መንግሥት እንዴት በአንድ ዓይን ማየትና በእኩል መታዘዝ ይቻላል? የሚል ነው። ለዚህ ተገቢ የሚሆነው መልስ ጳውሎስና ጴጥሮስ ከላይ ያየነውን መልዕክት ሲጽፉ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት ማየት በቂ ነው። ይህ መንግሥት በጭቆናው ወደር የሌለው የሮም መንግሥት ሲሆን፥ ሥልጣን ጨብጦ የነበረውም ቄሳር በጣም ነውረኛ ጨቋኝ፤ በእብደቱ የታወቀ፤ ክርስቲያኖችንም አጥብቆ የሚጠላ፥ ጳውሎስና ጴጥሮስን ጨምሮ ከቁጥር በላይ የሆኑ ክርስቲያኖችን በግፍ ያስገደለው ኔሮ (Nero) ነበር። የኔሮን ሁኔታ ጳውሎስና ጴጥሮስ ቢያውቁም ለክርስቲያኖች የጻፉት ትእዛዝ ግን መታዘዝ እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው።

ወደ ሥልጣን የሚመጡት መልካምም ክፉም ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሥልጣን ግን በራሱ መልካም ነው፤ ምክንያቱም፤ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው። ይህንን በተገቢው ለመረዳት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥልጣን እንደ ምሳሌ ማየት ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአማኞች መሃል ተመርጠው ለሥልጣን የሚበቁ አሉ። የሚሾሙትም በቅንና በእውነት መንጋውን እንዲጠብቁና እንዲያገለግሉ እንጂ ዘራፊዎችና ለመንጋው የማይራሩ ክፉ ገዥዎች እንዲሆኑ ታስቦ አይደለም። በሁለት ሺህ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግን የተሰጣቸውን ሥልጣን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባልሆነ መንገድ የተጠቀሙና ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ምእመናንን ያሳዘኑና ያሳፈሩ መሪዎች ተነሥተዋል። ቢሆንም ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የሥልጣን ቦታ ትክክለኛና አሁንም ሆነ ወደ ፊት፤ ጌታችን

እስከሚመጣ ድረስ የሚሠራ ነው። የመንግሥት ሥልጣንም እንደዚሁ ነው። በሥልጣኑ ላይ የሚቀመጠው ክፉም በጎም ሊሆን ይችላል፤ ሥልጣኑ ግን ከላይ ነውና ትክክል ነው። ይህንንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ 19፡11 ላይ አረጋግጦልናል። እንደ ጲላጦስ ዓይነቱ ክፉ አእምሮ ያለው ገዢ በጌታ ላይ ሊፈርድ ያስቻለውን ሥልጣን ያገኘው ከላይ ነበር። ይህም የሚያሳየን በሕጋዊ መንገድም ይሁን ወይም በዓመፅ በሥልጣን ላይ የወጣን መንግሥት፤ ፍትሐዊም ይሁን ወይም ጨቋኝ የሆነውን ባለሥልጣን መታዘዝ የማንኛውም ክርስቲያን ግዴታ እንደሆነ ነው።

መንግሥት ላወጣው ሕግ ታዛዥና ተገዢ መሆን የክርስቲያን ሁሉ ግዴታ ነው ቢባልም ይህ መታዘዝ ግን በደፈናው ወይም በጭፍን የሚደረግ ከበላይ ባለሥልጣናት የመጣውን ሁሉ ሳያገናዝቡ መቀበል ማለትም አይደለም። ምንም እንኳን የባለሥልጣናት ትእዛዝ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ፈቃድና ከመልካም ኅሊና ጋር የሚቃረን ትእዛዝን መቀበል ተገቢ አይሆንም። ምንም ዓይነት አዋጅ ማስፈራሪያ ታጅቦ ቢወጣና ይህም ወደ ኀጢአት የሚከተን፤ መልካሙንም ኅሊናችንን የሚያጎድፍና የአምላካችንን ሕግ የሚያስጥሰን ከሆነ አንቀበልም ማለት ተገቢ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ክርስቲያን በመጀመሪያ ታማኝ ሆኖ መገኘት ያለበት ለእግዚአብሔር በመሆኑ ነው። እርሱም በግራ እጁ መንግሥትን ባስታጠቀው የሰይፍ ሕግ በኃጢአት ምክንያት የወደቀውን የሰውን ልጅ እያስተዳደረ ያለው፤ እንዲሁም በቀኝ እጁ ቤተ ክርስቲያንን ባስታጠቀው የፍቅር ወንጌል ፍጥረቱን ሁሉ ወደ ደኅንነት እያመጣ ያለ ነው። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አለመታዘዝ የሚገለጸው በዝምታ ወይም በመሸሽ ወይም መከራን በመቀበል ብቻ ነው ወይስ ተቃውሞ በማስነሣትና በዓመፅም ጭምር የሚል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ መታዘዝ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚነግረንን ያህል ስለ አለመታዘዝ አይነግረንም። ነገር ግን በቃሉ ውስጥ ተመዝግበው ባሉ ልዩ ልዩ ድርጊቶች ላለመታዘዝ መነሻ ምክንያት የሚሆኑትንና አለመታዘዝ በምን መልኩ እንደሚከናወን ተገልፆልናል። ለምሳሌም ዘጸአት 1፡15–21 ላይ የእስራኤላውያን መዋለድና መባዛት በፖለቲካ ሥልጣኑ ላይ ስጋት ያደረበት የግብፅ ፈርዖን፥ ዕብራውያንን ወንዶች ልጆች እንዲገደሉ ያወጣውን ትእዛዝ ለመቀበል የዕብራውያን አዋላጆች እንቢ አሉ። እንቢታቸውን የገለጹት ግን ጥበብ በተሞላበትና

የፈርዖንን ቁጣ በማይጋብዝ መልኩ ነበር። ይህንን የአዋላጆቹን እምቢታ እግዚአብሔርም ሲደግፈው በዚሁ ክፍል እንመለከታለን። ዳንኤል 3 ላይ ያሉት ሦስቱ አይሁዳውያን ለመንግሥት አዋጅ አንታዘዝም ያሉበትን መንገድ ስንቃኝ አለመታዘዛቸውን ፊት ለፊት በማሳየት ሊገጥማቸው የሚችለውንም የመንግሥት ቁጣ ለመቀበል በመዘጋጀት ላይ ያተኮረ ነበር። እዚህም ላይ የእግዚአብሔር ድጋፍ ተገልጧል። ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ ወንጌል እንዳይሰበክ የአይሁድ አለቆች ያወጡትን ትእዛዝ ሐዋርያት የጣሱትና አለመታዘዛቸውንም ያሳዩት ያንኑ የተከለከሉትን በግልጽ በማድረግ ነበር። ላለመታዘዝ ያበቃቸውንም ምክንያት ሲያስረዱ፣ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» በማለት እንደሆነ እናያለን (የሐዋ. 5፡27-29)። አለመታዘዝ የሚገለጽበት ሌላው መንገድ አካባቢን ትቶ ወደ ሌላ መሸሽ ወይም በስውር (underground) የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ሊሆን እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዱናል።

አለመታዘዝን በተመለከተ ብዙ ጊዜ የሚነሣው ጥያቄ፣ ባለመታዘዝ እግዚአብሔርን እንጂ ባለሥልጣናትን ወይም መንግሥትን እንዴት ማገልገል ይቻላል? የሚል ነው። ለዚህም መልስ የሚሆኑን ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ከላይ ያነሣናቸው ሦስቱ የዳንኤል ጓደኞች የባቢሎን መንግሥት ያወጣው አዋጅ ከባድ፣ አለመታዘዝም በሚነድ እሳት እቶን ውስጥ የሚያስጥል መሆኑን ቢያውቁም አንታዘዝም ብለው ጸንተው በመቆማቸው ምክንያት ወደ እሳት ውስጥ በተጣሉ ጊዜ (ዳን. 3)፣ እንዲሁም ዳንኤል የዳርዮስ መንግሥት ላወጀው አዋጅ ላለመታዘዝ ወስኖ አዋጁን በመጣስ የአምላኩን ሕግ በማክበሩ ምክንያት በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ በተጣለ ጊዜ (ዳን. 6)፥ አምላካዊው ክብር እንዲገለጥ፣ የነገሥታቱና የሕዝቡ ዓይኖች እንዲከፈቱና የእግዚአብሔርን ማንነት እንዲያዩ አልረዳቸውምን? እግዚአብሔርስ ክብሩን አልገለጠበትምን? ይህስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው ሥርዓት አንታዘዝም የማለታቸው ውጤት አይደለምን?

*መንግሥት ለሚያወጣው ትእዛዝ በመታዘዝና ባለመታዘዝ ጉዳይ ላይ ለቤተ ክርስቲያን እንደ መመሪያ የሚያገለግሉ ስድስት ነጥቦች።*

1. ለመንግሥት መታዘዝና ባለሥልጣናቱንም ማክበር፣ እንዲሁም የዜግነት ግዴጅን በአግባቡ መወጣት ከሰማያዊው ተልዕኮዋ ቀጥሎ ቤተ ክርስቲያን ማከናወን ያለባት አገልግሎት አድርጋ መቁጠር አለባት።

2. እምቢተኝነት ወይም አለመታዘዝ የሚመጣው የእግዚአብሔር ቃል አታድርጉ የሚለውን ማንኛውንም ነገር መንግሥት እንዲደረግ ሲያዝ፣ ወይም የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያንን እንድትፈጽም የሚያዛትን የሚከለክል ትእዛዝ መንግሥት ሲያዝ ብቻ ነው። ለምሳሌ መንግሥት ውርጃን (Abortion) የሚደግፍ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ማስተማር እንዳለባት ቢያዝ፣ ወይም ወንጌል እንዳይሰበክ የሚከለክልን ትእዛዝ ቢያውጅ፣ እንደዚህ ዓይነቱን ትእዛዝ አሜን ብሎ መቀበል አይቻልም።

3. መንግሥት ያዘዘው ትእዛዝ ከቆምንበት ሰማያዊ ዓላማ ጋር ስለሚቃረን ልንታዘዝ አንችልም የሚለው ውሳኔ መገለጽ የሚገባው፣ (ሀ) ተገቢው አቤቱታ በተገቢው መንገድ ለመንግሥት ከቀረበ በኋላ፣ (ለ) በውይይትም ሆነ በደብዳቤ ወይም በሌላ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚከሰተው የእምነት መፋለስ ለመንግሥት ከተጠቆመ በኋላ፣ (ሐ) የሕግ የበላይነት በተረጋገጠበት አገር ደግሞ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድና ጉዳዩ በዳኝነት እንዲታይም ከተደረገ በኋላ መሆን ይገባዋል።

4. አስፈላጊው የአቤቱታ መንገድ ሁሉ ባለመሳካቱ አለመታዘዝን የመረጠች ቤተ ክርስቲያን አልታዘዝም የማለት አካሄዱ ዓመፅን በማነሣሣት ሳይሆን ባለመታዘዝ ምክንያት የሚመጣውን ማንኛውንም ቅጣት ለመቀበልና ዋጋ ለመክፈል በመዘጋጀት ብቻ መሆን ይገባዋል።

5. የቤተ ክርስቲያን አለመታዘዝ ወይም ተቃውሞ ማተኮር የሚገባው መታዘዝ የለብኝም በምትለው ጉዳይ ላይ እንጂ የመንግሥት ሥልጣን ላይ መሆን አይገባውም።

6. በአለመታዘዝና በዚያም ምክንያት የሚመጣውን ዋጋ በመክፈልም ውስጥ እንኳ ቤተ ክርስቲያን ለባለሥልጣናት የምትሰጠውን ክበሬታና ለእነርሱ መጸለይን መተው አይገባትም።

በዚህ ክፍል ውስጥ ያየነው ለገዢዎች ወይም ለባለሥልጣናት በሚደረግ መታዘዝ እግዚአብሔር እንደሚከብር ሁሉ ባለመታዘዝም

እንደሚከብር ነው። እንደ ምሳሌ የወሰድነው ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ያለፉበትን ሁኔታ ሲሆን፥ እነዚህ ሰዎች መንግሥት ያወጣው አዋጅ የአምላካቸውን ሕግ የሚጥስ እንደሆነ ተረድተዋል፤ አዋጁን ቢጥሱ የሚደርስባቸውን አውቀዋል፤ ቢሆንም ውሳኔያቸው የመንግሥትን ትእዛዝ ጥሰው የአምላካቸውን ሕግ ማክበርና በዚያም የተነሣ የሚመጣባቸውን ቅጣት በጸጋ መቀበል ነበር። ይህ ዓይነቱ በአለመታዘዝ ምክንያት የሚመጣን የመንግሥትን እርምጃ ያለተቃውሞ የመቀበል አካሄድ «Passive resistance>> በመባል ይታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን አለመታዘዝን ተከትሎ የሚመጣውን ሁሉ ያለ ተቃውሞ መቀበልን የማይቀበሉ ወገኖች አሉ። እነዚህም በሁለት ይከፈላሉ፤ በአንደኛው ጎራ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚጋጨውን የመንግሥትን ትእዛዝ አለመቀበል ብቻውን በቂ ስለማይሆን አለመታዘዝን ንቃት ባለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ (Active resistance) በመግለጽ መንግሥት ያወጣውን የማይመች ሕግ እንዲለውጥ ጫና መፍጠር አለብን የሚሉ ናቸው። ይህንን አመለካከት የሚያራምዱ ክርስቲያኖች የሚሰጡት ምክንያት አንድ መንግሥት እግዚአብሔር ከሰጠው ኀላፊነት በመውጣት ክፉ አሠራርን ከተከተለና ወደ ጨቋኝነትና አምባገነንነት ከተለወጠ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ አድርገን ልንቆጥረውና ልንታዘዘው ቃሉም ሆነ ሕሊናችን አያስገድደንም የሚል ነው። የዚህ አቋም ደጋፊዎች፤ ፍትሐዊ ያልሆነ ሕግ እንደ ሕግ ሊቆጠር ፈጽሞ አይገባውም የሚለውን የ13ኛውን ክፍለ ዘመን የሥነ መለኮት ሊቅ የቶማስ አኪዊናስን (Thomas Aquinas) አስተምህሮ ለእንቅስቃሴያቸው ድጋፍ ይጠቀሙበታል።

መንግሥት ፍትሐዊነትን ጥሎ ጨቋኝ ሲሆን፣ ማኅበራዊ ቀውስን የሚያባብሱ ለዘረኝነትና አላስፈላጊ ለሆነ ጦርነት በር የሚከፍቱ ሕጎችን ሲያወጣ፤ አለመታዘዛችንን ንቁ በሆነ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መግለጽ አለብን ብለው ያምናሉ። ይህም የሚከናወነው ተቃውሞን አደባባይ ይዞ በመውጣት በሰላማዊ ሰልፍና በሌሎችም ሰላማዊ በሆኑ የተቃውሞ መግለጫዎች በመንግሥት ላይ ጫና በመፍጠርና ሕዝብን በማንቃት ነው። ከዚህም ጋር አያይዘው ተቃውሞው ኃይልን ባለመጠቀም (Non-violent) መንገድ የሚገለጽ በመሆኑ

ከመንግሥትም ሆነ ከባለሥልጣናት ሊመጣ የሚችለውን አእምሮአዊና አካላዊ ጥቃት በጸጋ ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣ እንዲሁም ከጥላቻና ከበቀል የራቀ አቋም መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ። የዚህ እንቅስቃሴ ዋነኛ ትኩረት ተገቢ ያልሆነው ሕግ እንዲለወጥ እንጂ መንግሥትን ለመለወጥ መታገል አይደለም። ኃይልን ባለመጠቀም የሚገለጽ እንዲህ ዓይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ «Non-violent resistance>> በመባል ይታወቃል።

ይህ እንቅስቃሴ ሲነሣ አብረው የሚነሡት እውቁ የቤተ ክርስቲያን መሪና የአሜሪካ ጥቁሮች መብት ተሟጋች የነበሩት ማርቲን ሉተር ኪንግ ናቸው። ማርቲን ሉተር ለእንቅስቃሴያቸው እንደ ተምሳሌት የተጠቀሙት የሕንዳዊውን የማህተመ ጋንዲን አስተምህሮ (Satyagraha) ነበር። ጋንዲ ያለ ወታደርና ያለ ጠመንጃ፣ በሰላማዊ ተቃውሞ ብቻ የሕንድን ሕዝብ ከእንግሊዝ የጭቆና አገዛዝ ነፃ እንዳወጡ ሁሉ፥ ማርቲን ሉተር ኪንግም ሰላማዊ ሰልፎችንና ልዩ ልዩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በተከለከሉም ሆነ ባልተከለከሉ ስፍራዎች በማካሄድ የአሜሪካንን ጥቁሮች እንደ ሁለተኛ ዜጋ ያስቆጥር ከነበረው ጨቋኝ ሕግ ነፃ አውጥተዋል።

ሁለተኛዎቹ ወገኖች ከመጀመሪያዎቹ ጋር በብዙ ነገር ይስማሙና ነገር ግን፣ የተቃውሞ እንቅስቃሴን በሰላማዊ መንገድ ብቻ ማካሄድ በሚለው ጉዳይ ላይ ይለያያሉ። እንደ እነዚህ ወገኖች አመለካከት በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ የሚደረግ ተቃውሞ ውጤት ካላመጣ ኃይልን በመጠቀም ተቃውሞን መግለጥ (Violent resistance) እንደ መጨረሻ አማራጭ መወሰድ አለበት ይላሉ። የሰው ደኅንነት ሙሉ የሚሆነው ካለበት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጭቆና ነፃ ሲወጣ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ለዚህ እምነታቸው እንደ ማስረጃ የሚጠቅሱት ኦሪት ዘፀአት 1-14 ላይ ያለውን እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበትን እንቅስቃሴ ነው። በዚያን ሰዓት እስራኤላውያንን ነፃ ለማውጣት ከሙሴ ጎን የቆመ እግዚአብሔር ዛሬም የተጨቆኑትን፣ የተገፉትንና ድሆችን ከዘመኑ «ፈርዖኖች» ለማዳን በሚደረግ እንቅስቃሴ ጎን ይቆማል ብለው ያምናሉ።

እነዚህ ክፍሎች በዐመፅ የሚመጣ አብዮትንም (Violent-Revolution) ከመደገፋቸውም በላይ በእነዚህ ሰውን ከጭቆና ነፃ ለማውጣት በሚደረጉ ሕዝባዊ ትግሎች ውስጥ ተካፋይ የሚሆን ክርስቲያን በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ እንደተካፈለ ሊቆጥር እንደሚገባና ቤተ ክርስቲያንም ይህንን መደገፍ እንዳለባት አጥብቀው ይከራከራሉ። ይህ እንቅስቃሴ «Liberation Theology» (ሊበሬሽን ቲዎሎጂ) በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ በ1960ዎቹ በደቡባዊ አሜሪካ አገሮች ከጭቆና አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ይደረጉ የነበሩትን ሕዝባዊ ትግሎች ይደግፉ የነበሩ የካቶሊክና ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የነደፉት፣ ትግሉ ሥነ መለኮታዊ (Theological) ድጋፍ እንዲኖረው ታስቦ የተቀመረ ነበር። ሊበሬሽን ቲዎሎጂ ለእኩልነት ይታገሉ በነበሩት የአሜሪካ ጥቁሮች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ሲሆን፥ ከቅኝ አገዛዝና ከጭቆና ነፃ ለመውጣት ይታገሉ ወደነበሩት አፍሪካውያንና እስያውያንም ዘንድ ተዛምቶ ነበር። ወደ አፍሪካ ሲመጣም በአፍሪካ ካለው የጭቆና ዓይነትና የትግል ስልት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ጥቂት ለውጥ ከተደረገለት በኋላ «Black Theology» (ብላክ ቲዎሎጂ) በሚል ስያሜ ይጠራ ነበር።

አለመታዘዝ በኃይል ሳይሆን ሰላማዊ በሆነ የተቃውሞ መንገድ መገለጽ ይገባዋል የሚለውን የመጀመሪያዎቹን ወገኖች አቋም በተለያዩ ቤተ እምነቶች (Denomination) ድጋፍ ያለው ሲሆን፥ ተቃውሞን በኃይልም ጭምር ማድረግ አለብን የሚሉትን የሁለተኛዎቹን ወገኖች አቋም ግን ብዙዎች ክርስቲያኖች በተለይም ወንጌላውያን አማኞች አይቀበሉትም። ለዚህም ምክንያቱ ይህ አቋም በማቴዎስ 26፡52 ላይ ያለውን «ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ» የሚለውን የጌታን ማስጠንቀቂያ የጣሰና መስቀሉን በሰይፍ የለወጠ አቋም በመሆኑ ነው።

አስቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥሎም ሐዋርያት የተዉልን ምሳሌ ዓመፅ እንደ አማራጭ እንዲሆን የሚያነሣሣ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ የነበረበትን ፖለቲካዊ ሁኔታ (political environment) ስንቃኝ የተወለደባት አገር ፓለስታይን የሮም መንግሥት የቅኝ ግዛት አካል ነበረች። ከዚህም የተነሣ በአንድ በኩል የቅኝ አስተዳደር (Colonial administration) የተሰየመላት፤

ጲላጦስን የመሳሰሉ ገዢዎች ከሮም ይሾሙላት የነበረ፣ የሮማውያን ጦር የሰፈረባት ምድር ነበረች። በሌላ በኩል ደግሞ በግድ የተጫነባቸው የሮም አገዛዝ ያንገሸገሻቸው አይሁዳውያን የነበሩባት፣ ቀናኢ (Zealots) ይባሉ የነበሩ የሮምን አገዛዝ በኃይል ለመጣል ዓመፅ ያካሂዱ የነበሩ ወገኖች የነበሩባት ምድር ነበረች። ሆኖም፣ ምንም እንኳን አይሁዳውያን ወገኖቹ የነበሩበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ጌታ የተገነዘበ ቢሆንም ይህንን ሁኔታ በኃይል ለመለወጥ ሲነሣ፣ ወይም ዐመፅ ሲያካሂዱ ከነበሩት ኃይሎች ጋር ሲተባበር አልታየም።

በታሪክም የታየው በዚህ ዓይነት ዓመፅ የመጣ ለውጥ ብዙ ሕይወትን ያጠፋ፣ መፈናቀልንና ምስቅልቅልን ያስከተለ ነበር። ከዚህም በላይ ብዙ ጊዜ እንደታየው በዓመፅ ሥልጣን ላይ የወጣው ወገን አስቀድሞ ከነበረው ይልቅ የባሰ ጨቋኝ ሆኖ ይለወጣል። እንደ ምሳሌም የፈረንሳይንና የራሺያን አብዮት እንዲሁም በተለያዩ አገሮች የተካሄዱ አብዮቶችን ስንቃኝ ለስኬታቸው የጠፋው ሕይወትና ንብረት ቀላል ካለመሆኑም በላይ ሥልጣን የተረከቡትም አስቀድመው ከነበሩት ይልቅ የባሰ ጨቋኝ ሲሆኑ ተስተውሏል። በአገራችንም በ1966 ዓ.ም በተካሄደው አብዮት ሥልጣን ይዞ የነበረውና ፍትሕን፣ እኩልነትንና እድገትን ሊያመጣልን ቃል የገባው የደርግ ሥርዓት ከሥልጣን ካወረዳቸው ንጉሥና መሳፍንት ሰባት እጥፍ ብሶ አይተናል።

ሊበሬሽን ቲዎሎጂ የበለጠ አትኩሮት የሚሰጠው፣ ሰው በወንጌል ኀይል ከኃጢአት ባርነት ነፃ መውጣቱ ላይ ሳይሆን፥ ሰው ከጭቆና አገዛዝ ነፃ መሆኑ ላይ በመሆኑ ከኮሚኒዝም ጋር ሲመሳሰል፥ እንቅስቃሴውን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋ ማጀቡ ክርስቲያናዊ ያስመስለዋል። የሥነ መለኮት ሊቃውንት «Communism with a Christian face» (ክርስቲያናዊ ገጽታ ያለው ኮሚኒዝም) በማለት ይተቹታል። እንደገናም ሊበሬሽን ቲዎሎጂ ትኩረት የሚሰጠው ኅብረተሰብን ለመለወጥ በሚደረግ ብዙ ጥፋትን በሚያስከተል የትግል ስልት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን በእንዲህ ያለ እንቅስቃሴ ውስጥ እጇን መክተት አይገባትም። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያተኩረው እንደ አብዮት ኅብረተሰብን ለመለወጥ በሚደረግ የትጥቅ ትግል ሳይሆን፥ የኅብረተሰቡ ዋነኛ መሠረት የሆነውን ግለሰብን በወንጌል ኃይል በመለወጥ ነው። አንድ ሰው ሲለወጥ አጥፊ ለሆነው ራስ ወዳድ መሻቱ መገዛቱን ያቆማል፤ ለራሱ ብቻ

ሳይሆን ለሌሎችም ማሰብ ይጀምራል፤ ተግባሩን ሁሉ እግዚአብሔርን ከማገልገል ጋር ያያይዛል። እንዲህ ዓይነት የተለወጡ ሰዎች እየበዙ ሲሄዱ፣ ወደ ኅብረተሰቡም ውስጥ እየዘለቁ ሲገቡ፣ ያን ጊዜ እውነተኛና ለእግዚአብሔር የሚገዛ ኅብረተሰብ ይፈጠራል። በዚህን ጊዜ ነው የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት በመካከላችን ናት ብለን በድፍረት መናገር የምንችለው።

## ማጠቃለያ አሳብ

ቤተ ክርስቲያን ስለ መንግሥት የምትረዳው የማያምኑት በሚረዱበት ዓይነት ማለትም እንደ ምድራዊና ሰዋዊ ተቋም ብቻ አድርጋ መሆን የለበትም። ምክንያቱም የመንግሥት መሥራችና የሥልጣኑም ዋንኛ ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን፥ እንዲሁም ተልዕኮውም ሆነ ተግባሩ መለኮታዊ ዓለማ ያለው መሆኑን ትረዳለችና ነው። በዚህም መነሻነትና ቤተ ክርስቲያንም የመንግሥት (state) አካል በመሆኗ አመቺ በሆነው የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የበኩሏን ተሳትፎ ማድረጓ ጠቃሚ ነው። ተሳትፎዋን በትጋት የምትወጣ ቤተ ክርስቲያን፤ አንደኛ፣ የመንግሥት ሥልጣን በውክልና ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንጂ የራሱ እንዳልሆነና የምድር ነገሥታት ሁሉ ገዢና የበላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ (ራእ. 1፥5)፤ ሁለተኛ፣ በዓለም ያለው ሁሉ፣ ፖለቲካንም ጨምሮ በክርስቶስ የአገዛዝ ሥልጣን ሥር እንዳለ ምስክር መሆን ትችላለች።

በተቃራኒው ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት በኅብረተሰቡ የፖለቲካ ሕይወት ላይ እንዳይንጸባረቅ መከላከል፤ አንደኛ፣ ፖለቲካን ሁሉ ለእርሱ እና በእርሱ የሆነው ከክርስቶስ የጌትነትና የሥልጣን (ማቴ. 28፥18–20) ክልል ውጭ እንደሆነ መቁጠር ይሆናል። ሁለተኛ፣ የፖለቲካን ሕይወት በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለክርስቶስ እንዲገዛ ከመማረክ ይልቅ (2ኛ ቆሮ. 10፥3–6) ለማያምኑና በክፉው ለሚመሩ ሰዎች ነፃ ግዛት አድርጎ እንደመተው ይሆናል። የፖለቲካውን ዓለም የክርስቶስ ኀይልና ጌትነት ሊደርስበት የማይችል ለብቻ ተገልሎ ያለ ወይም የሰይጣን ነፃ ግዛት አድርጎ መተው የክርስቶስን ሁሉን ገዢነት ከልብ አምኖ አለመቀበልና የሥልጣኑንም አድማስ አሳንሶ የማየት ያህል የከፋ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሊመጣ ያለው ዓለም ብቻ ሳይሆን አሁን ያለንበት ዓለምም ጌታና ሁሉ ከእግሩ በታች ሊገዛለት የተገባው አምላክ ነው (ኤፌ. 1፥19–23)።

# ክፍል ሁለት

## ክርስቲያንና ፖለቲካ

በክፍል አንድ ውስጥ መንግሥትን ለማገዝ የሚደረጉ የቤተ ክርስቲያንን ትርጉም ያለው ተሳትፎ አይተናል። ይህ ተሳትፎ ግን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም የአንድ የፖለቲካ ቡድን ደጋፊ፤ የፖለቲካ አቋሙም ማራማጃ መድረክ መሆንና ለሥልጣን እንዲበቃ መሯሯጥ፤ ወይም በፖለቲካ ውሳኔዎች ውስጥ ጣልቃ በመግባት ጫና ለማሳደር መሞከር ማለት አይደለም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሣው ጥያቄ፤ ቤተ ክርስቲያን ከተሳጣት ተልዕኮ የተነሣ በፖለቲካ ውስጥ የሚኖራት ተሳትፎ ውሱን ቢሆንም፥ አማኞች ግን በግላቸው በፖለቲካ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ቢያደርጉ ምን ችግር አለበት? የሚል ነው። ይህንን በተመለከተ ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች ያሉ ሲሆን፥ እነዚህንም ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 1. ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ስለመሳተፉ የሚሰጡ አስተያየቶች

የክርስቲያንን በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍን የሚደግፉ እንዳሉ ሁሉ አጥብቀውም የሚቃወሙ አሉ፤ ከተቃዋሚዎቹ ወገን ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ለምን መግባት እንደሌለበት ተዘውትረው የሚነሡትንና እንደ መከራከሪያ ከሚቀርቡት ውስጥ ዋና ዋና የሆኑትን፤ በማያያዝም እነዚህ በምክንያትነት የሚቀርቡት ተገቢ በሆነ ግንዛቤ ላይ እንዳልተመሠረቱና የሚያስተላልፉትም መልእክት የተዛባ እንደሆነ እንደሚከተለው እናያለን።

በመጀመሪያ ይህ ዓለም በክፉው የተያዘ በመሆኑና የምንከተለው ክርስቶስም ከዚህ ዓለም እንዳይደለ ሁሉ ክርስቲያንም ከዚህ ዓለም ባለመሆኑ (1ኛ ዮሐ. 5፡19፤ ዮሐ. 17፡14)፤ በዚህ ዓለም ካለው ዕድፍ ራስን መጠበቅ እንጂ ከዓለም ጋር መደባለቅ ክርስቲያናዊ ምግባር መሆን እንደሌለበት (ያዕ. 1፡27) መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል በሚል የክርስቲያንን በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ ከሚቃወሙት ወገኖች መከራከሪያ ሆኖ ይቀርባል።

ከተቃዋሚ ወገኖች እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች መዝዞ በማውጣት በእንዲህ መልኩ ለመከራከሪያነት ቢያቀርቡዋቸውም፤

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስጠንቀቂያዎች በትክክል ለተረዳ ክርስቲያን የሚሰጡት ትርጉም ግን እነርሱ እንደሚሉት አይደለም። አንድ ክርስቲያን ያለ ክርስቶስ ተደራጅቶ (organized) በሚኖረው ኅብረተሰብ ውስጥ ከሚንጸባረቁት፣ ከሰማያዊው መንግሥት አሳብ ጋር ከማይጣጣሙ ባህሎች፣ አመለካከቶችና የኑሮ መመሪያዎች ራሱን መለየት እንዳለበት፣ ነገርን ሁሉ የሚለካበት መንገድም (value system) የተለወጠና በዓለም ካሉት፣ ሰማያዊ ብርሃን ካልበራላቸው ሰዎች የተለየ መሆን እንዳለበት የሚያሳስቡ ቃሎች እንጂ፥ የሚኖርበትን ዓለም ወይም ኅብረተሰብ እርግፍ አድርጎ በመተው ተገልሎና አያገባኝም በሚል በሩን ዘግቶ እንዲቀመጥ የሚያስጠነቅቁ አይደሉም። ይህ አካሄድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስጠነቅቀውና መብራትን አብርቶ በዕቃ ውስጥ እንደ መሸሸግ የሚቆጠር ነው (ማቴ. 5፡15)። ከዚህ ዓለም ያለመሆናቸው ጉዳይ በትክክል የገባቸው ክርስቲያኖች ግን «ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት የበራ ይሁን» (ማቴ. 5፡16) የሚለውን የጌታን ትእዛዝ አንግበው የአገራቸውን የፖለቲካ ሁኔታ ለመለወጥ በሚችሉት ሁሉ ቢሳተፉ ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ።

ሌላው ተቃዋሚዎች የሚያነሡት መከራከሪያ ደግሞ የክርስቲያን አገር በሰማይ በመሆኑና ዜግነቱም ሰማያዊ በመሆኑ (ፊልጵ. 3፡20) በላይ በሰማይ ላለው እንጂ ለምድራዊ ዜግነቱ መጨነቅና ማሰብ ስለሌለበት (ቆላ. 3፡2) በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ መጠላለፍ የለበትም የሚል ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አንድ ሰማያዊ ዜግነቱ በትክክል የገባውና አገሬ በሰማይ ነው ብሎ ጸንቶ የቆመ ክርስቲያን፣ ምድራዊ ዜግነቱ የሚጠይቅበትን፣ ለአገሩና ለኅብረተሰቡ ሊያበረክተው የሚገባውን የበኩሉን ድርሻ ከማድረግ ወደ ኋላ ሊል አይችልም። በምሳሌነት የምናነሣቸውም፣ አገራቸው ባልሆነ አገር፣ ሕዝባቸውም ባልሆነ ሕዝብ መካከል ታላቅ ኀላፊነት ተቀብለው አስደናቂ ሥራ የሠሩትን እንደ ዮሴፍ፣ ዳንኤልና መርዶክዮስን የመሳሰሉትን የእግዚአብሔር ሰዎችን ሲሆን፤ የስኬታቸው አንዱ ምሥጢርም ሰማያዊውንና ምድራዊውን ዜግነታቸውን በታማኝነትና ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ መያዝ መቻላቸው ነው። እንደዚሁም፣ አንድ ክርስቲያን ምድራዊ ዜግነቱን ማጣጣል

ሳይሆን ጥሩ ዜጋ ለመሆን፣ በዜግነቱም ሊወጣው የሚገባውን ድርሻ ሁሉ በትጋት ሊወጣ መጣር አለበት። በንግድ፣ በህክምና፣ በትምህርት፣ በሕግ ሙያ ወይም በሌላ በማንኛውም የሙያ ዘርፍ የተሰማራ ክርስቲያን ዜጋ ማድረግ የሚጠበቅበትን ብርሃንና ጨው የመሆንን ተግባር በፖለቲካው ዘርፍ የተሰማራ ክርስቲያን ዜጋም በክርስትና መመሪያ ላይ ተመሥርቶ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ በመሳተፍ እንዲሁ ከማድረግ የሚከለክለው አንዳች ነገር አይኖርም።

ከተቃዋሚዎች ዘንድ በብዛት የሚደመጠው ሌላው ጉዳይ ደግሞ «ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው» («Politics is a dirty game>>)፥ በመሆኑም ክርስቲያን ለሆነ የሚመች ስፍራ አይደለም የሚል ነው። ይህንን በበለጠ ሲያብራሩት፣ አንድ ሰው የተዋጣለት ፖለቲከኛ ለመሆን መዋሸትን፣ ሊፈጽመው እንደማይችል ልቡ እያወቀ የማይሆን ቃል መግባትን፣ ማንኛውንም ዓይነት መንገድ በመጠቀም ተቀናቃኞቹን ለማሳጣትና ለመጣል መሞከርን፣ ሌሎችን መጠቀሚያ አድርጎ የራሱን ሥልጣን ማጠናከርንና እነዚህን የመሳሰሉትን የከፉት ተግባራትን መፈጸምን ይጠይቃል፤ ስለዚህም አንድ ክርስቲያን በአንድ በኩል ይህንን እያደረገ በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቲያን ነኝ ማለት ፈጽሞ አይችልም በማለት በፖለቲካ የመሳተፍን አደገኝነት ይጠቁማሉ።

ይህ አባባል በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ያለውና አንድ በፖለቲካ ውስጥ የገባ ክርስቲያን ይህንን ሁሉ የሚያደርግ ከሆነ በክርስትና ሕይወት ውስጥ አለ ለማለት በእርግጥም አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ፖለቲካን ቆሻሻ የሚያሰኘው ሰማያዊ ብርሃን ባልበራላቸው፣ በዚህ በከፉው በተያዘው ዓለም ተመን (Value) በሚመሩ ሰዎች የተሞላ ከመሆኑ የተነሣ እንጂ ፖለቲካ በራሱ የሚያመጣው በመሆኑ አይደለም። ይህ ደግሞ በፖለቲካው ክፍል ውስጥ ጎልቶ ይታይ እንጂ በሌሎቹም የሙያ ዘርፎች ያለና የተለመደ ገጽታ ነው። ፖለቲካ «ቆሻሻ» ነው ሲባል በጨለማ የተዋጠ ወይም በክፉው የተያዘ ማለታችን መሆን አለበት፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህን በፖለቲካው ዓለም ውስጥ አለ የምንለውን መጥፎ ገጽታ አውቀን ዝም ከማለት ይልቅ እንዲለወጥ መጣሩ የበለጠ ይጠቅማል። ለዚህ ተግባር ደግሞ ብርሃንና ጨው ሆነው ለመለወጥ የሚነሣሡ ሰዎች ማስፈለጋቸው አጠያያቂ አይሆንም። ለእንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት መለኮታዊ ጥሪ ያላቸው፣ አስፈላጊው ትጥቅ የተሰጣቸው ደግሞ ክርስቲያኖች ናቸው። ይህም

የተሳትፎአቸውን አስፈላጊነት ጉልህ ያደርገዋል። በተቃራኒው ግን ክርስቲያኖች ከፖለቲካ መድረክ ራሳቸውን ሲያርቁ ብርሃን የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ከዚህ በከፋው ተይዟል ከምንለው ስፍራ ማራቃቸው አይደለም? ፖለቲካንስ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ከተባለው የዓለም ክፍል ውስጥ የማይቆጠር፣ ከመንፈስ ቅዱስ የሚመነጨው ክርስቲያናዊ ፍሬ ሊገለጥበት የማይችል፣ የክርስቶስም ገዢነት የማይደርስበት ስፍራ አድርገን መቁጠራችን አይደለም?

አንዳንዶች ደግሞ የክርስቲያኖችን በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍን ጉዳይ ቢደግፉትም የሚያሳስባቸው ግን፣ አብረው የሚሠሩት በአብዛኛው ከማያምኑ ጋር በመሆኑና ቁጥራቸውም አነስተኛ ስለሚሆን በፖለቲካው ውስጥ ይህ ነው የሚባል ለውጥ ከማምጣት ይልቅ በማያምኑት በብዙሀኑ ስለሚዋጡ ብርሃን መሆን ይቅርና ያላቸውንም የክርስትና ሕይወት የሚያስጥላቸው ሁኔታ ሊኖር ይችላል የሚል ነው፤ ስለዚህም በፖለቲካ ውስጥ ከመግባት ይልቅ አለመሞከሩ ይሻላል የሚል መከራከሪያ ያነሣሉ።

የእነዚህኞዎቹ መከራከሪያ ነጥብ እግዚአብሔር አንድ ወይም ጥቂት ተራ (ordinary) ሰዎችን ተጠቅሞ ታሪክን የሚለውጥ አምላክ መሆኑን ካለመገንዘብ የመነጨ ነው። አንድ ሙሴን ተጠቅሞ ገናና የነበረውን የፈርዖንን መንግሥት ገለባብጦ በባርነት ይማቅቅ የነበረውን ሕዝቡን እስራኤልን ነፃ ያወጣ፤ ንግሥት አስቴርን ተጠቅሞ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ለጥፋት የታወጀን አዋጅ ያስገለበጠ፤ በዳንኤልና በሦስቱ ጓደኞቹ ተጠቅሞ ምርኮ በነበሩበት ምድር ክብሩንና ኀያልነቱን የገለጸ እግዚአብሔር ነው። ከዚህ የምንረዳው የእግዚአብሔር ጉዳይ ከቁጥር ጋር ሳይሆን ለሥራው የተሰጡና የታመኑ ሰዎችን ከማግኘቱ ላይ እንደሆነ ነው። ከዓለም ታሪክም የምንማረው በአሸናፊነት ብቅ ያሉ የታላላቅ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች (Political movements) ስኬት ምክንያት ለተነሡበት ዓላማ የተሰጡና በጽናት የቆሙ የጥቂት ሰዎች ብርቱ ጥረት እንደሆነ ነው። እንግዲህ መለኮታዊ ጉልበት ያልታከለባቸው፣ በሰብአዊ ጥረት ብቻ የተከናወኑ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ከሆኑ፣ እግዚአብሔር የተጨመረበት እንቅስቃሴስ እንዴት አብልጦ ውጤታማ አይሆን?

## 2. ክርስቲያን ሊሳተፍባቸው የሚገቡ የፖለቲካ ሂደቶች

በአገራችን የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ በተፈጠረው ክፍተት በመግባት የፖለቲካ ተቋማትን በመለወጥ የሕዝብ ለቅሶ እንዲያበቃ ለማድረግ ፈቃደኞች የሆኑ ሠራተኞችን እግዚአብሔር እየፈለገ ያለበት ዘመን ላይ ያለን ይመስላል። ለዚህም መለኮታዊ ጥሪ ምላሽ መስጠት የአማኙ ፋንታ ነው። ይህንን ጥሪ በትክክል የተረዱና ተገቢውን ምላሽ የሰጡ አማኞች በመንግሥት ኀላፊነት ውስጥ እየበዙ ሲሄዱ ሕዝብን ደስ የሚያሰኝ ለውጥ መከሰቱ አይቀርም። ይህንን ሁኔታ መጽሐፈ ምሳሌ 29፡2 እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡– «ጻድቃን በበዙ ጊዜ ሕዝብ ደስ ይለዋል፤ ኀጥአን በሠለጡኑ ጊዜ ግን ሕዝብ ያለቅሳል»።

አንድ ክርስቲያን በአገሩ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ተገቢና ኀላፊነት የተሞላበት ተሳትፎ ማድረግ የሚችልባቸው ልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች ያሉ ሲሆን፥ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ. መረጃ ማግኘት

አንድ አማኝ በአገሩ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ በቂ፤ ሚዛናዊና ትክክለኛ መረጃ (Information) ሊኖረው አስፈላጊ ነው። ይህ መረጃ በፖለቲካ ውስጥ ለሚኖረን ቀጥተኛ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ለአገርና ለመሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ለምናቀርበው ጸሎትም ጠቀሜታ አለው። የነህምያን ጾምና ጸሎት እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ፤ መነሻ ምክንያቱ ስለ ወገኑ እና ስለ አገሩ (ኢየሩሳሌም) ጠይቆ ካገኘው ትክክለኛ መረጃ የተነሣ እንደ ነበር እናያለን (ነህ. 1፡1–4)። አንድ ክርስቲያንም በአገሩ ማንኛውም ጉዳይ ላይ የሚኖረው አቋም በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል። በመረጃ ላይ የተመሠረተ አቋምም በእግዚአብሔር ቃል መፈተሽ ያለበት ሲሆን፥ ይህም የስሕተት አቋም ከመያዝ ይጠብቃል።

### ለ. በምርጫ መሳተፍ

አንድ ሰው በአገሩ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ጠቃሚ ሚና መጫወት የሚችልበት ቀላሉ መንገድ የፖለቲካ መብቱን ተጠቅሞ በተለያዩ ደረጃዎች በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ በመራጭነት መሳተፍ ነው። በመራጭነት መሳተፍ ጥንቃቄን የሚጠይቅና የሚመርጡትንም በግልም ሆነ በፓርቲ የቀረበ ተወዳዳሪ (Candidate) ብቃትና

የያዘውን አሳብ ጠቃሚነት አስቀድሞ ማጤን ያስፈልጋል። ዓለማችን ሥልጣንን መጠቀሚያ በማድረግ ለራሳቸው ክብርና ዝና ለማግኘት ከምንም በላይ የሚጠሙ፣ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሌሎችን ወደ ጎን ገፍተው ወደ ላይ ለመውጣት የሚጥሩ ሰዎች ያሉባት ናት። ስለዚህም በቅን ለማገልገል ከመፈለግ ውጭ ለግላዊ ጥቅም የሚሮጡትን በጥንቃቄ መለየት መቻል ይገባል። እዚህ ላይ ሊነሣ የሚችለው ትልቁ ጥያቄ ይሄ እንዴት ይቻላል? የሚል ነው። ከመልካም ጎሊና ለሚነሣ ክርስቲያን ይህ ነገር አስቸጋሪ አይሆንበትም፤ ምክንያቱም ለእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የሚታገዝበት ጸሎት የሚባል መሣሪያና ሌላውን የሚመረምርበት ልዩ የሆነ ትጥቅ ያለው በመሆኑ ነው።

## ሐ. ሕዝባዊ ማኅበራትን በማቋቋም

እነዚህ ማኅበራት የፖለቲካ ፓርቲ ዓይነት አቋም የሌላቸውና ለሥልጣን የማይወዳደሩ ሲሆኑ፤ አንድ ዜጋ የፖለቲካ ሥልጣን ሳይዝ ነገር ግን በአገሩ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ጠቃሚ ሚና እንዲኖረውና በመንግሥት ላይ ገንቢ የሆነ ጫና ማሳደር የሚያስችሉት ማኅበራት (Pressure groups) ናቸው። እነዚህ ማኅበራት በሁለት ይከፈላሉ፤ አንደኛው ቡድን፣ ከግል ጥቅም ጋር በተያያዘና የመንግሥት ሥልጣን በአንድ በሚፈልጉት ቡድን እንዲያዝ ከመፈለግ የተነሣ የሚቋቋሙ ሲሆን፣ በልዩ ልዩ መንገድ የሕዝብ ስሜት ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት በማሳጣት በውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር የሚጥሩ ናቸው። ሁለተኛው ቡድን ደግሞ፣ ከግል ጥቅም ጋር ባልተያያዘ መልኩ እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ ለአገርና ለወገን የሚጠቅሙ ለውጦች እንዲመጡ በመንግሥት ላይ አዎንታዊ ጫና ለማሳደር የሚቋቋሙ ናቸው።

እውቀትና ልምድ ያካበቱ፣ ለአገራቸውም መልካም ራእይ ያላቸው ክርስቲያኖችም እንደ ሁለተኛዎቹ ዓይነት ጠቃሚ ማኅበራት ማቋቋም ይችላሉ። በትምህርት፣ በጤና፣ በሕግ፣ በንግድና በሌሎችም የሙያ መስክ የተሰማሩና የእምነት አንድነት ያላቸው ከተሰማሩበትና ተገቢው እውቀት እንዳላቸው ከሚተማመኑበት የሙያ መስክ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ማኅበራት ሥር ተሰባስበው መንግሥትንና ኅብረተሰቡን እየተፈታተኑ ባሉ ችግሮች ላይ ጥናት በማድረግና ጠቃሚ

የሚኗቸውን የመፍትሔ ሐሳቦችን (proposals) ለመንግሥት በማቅረብ በሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ ይችላሉ። በተጨማሪም ለተጠቁ እና ሰሚ ላጡ ወገኖች በመቆም ሙያዊ እርዳታቸውን ማድረግ ይችላሉ። ይህ የቡድን ሥራ ለየብቻ ከሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝና ከማንም ሳይወግኑ በመልካም ኅሊና ከተከናወነ የመንግሥትንም ሆነ የኅብረተሰቡን ትኩረት መሳቡ አይቀርም። በእንዲህ በመሳሰሉ ማኅበራት ውስጥ ተሰባስበው የበኩላቸውን የዜግነት ግዴታቸውን የሚወጡ ክርስቲያኖች ዋነኛ መመሪያቸው ማድረግ የሚገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ ሲሆን፥ ራሳቸውንም ማየት የሚገባቸው እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ይገባዋል።

## መ. የፓርቲ አባል በመሆን

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝና ለመምራት በሚል ዓላማ የሚደራጁባቸው ቡድኖች ናቸው። በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ፓርቲዎች ለሕዝብ ይጠቅማል የሚሉትን ፕሮግራም በመቅረጽና ለሕዝብ በማቅረብ ለሥልጣን ይወዳደራሉ፤ ካሸነፉም አገርን የመምራት ኀላፊነትን ይቀበላሉ። ከዚህም በተጨማሪ አገርን የሚመሩ ብቁ መሪዎችን በማፍራት፣ ሕዝቡ ስለ ፖለቲካ ሁኔታዎችና ሂደቶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግ፣ በተቃዋሚነት ሚናቸው በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት አካሄድ በቅርብ በመከታተልና ስሕተቶቹን ለሕዝብ በመጠቆም፥ እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት በማገዝ ተግባር ላይ የሚሰማሩ ተቋማት ናቸው።

ክርስቲያኖች በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ተሳትፎ ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ሁለት ዓይነት መንገዶች አሉ፤ አንደኛው መንገድ የፓርቲ አባል በመሆን ነው። የዲሞክራሲን ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የሚገኙ ፓርቲዎች የሚመሩባቸው በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያላቸው እኩልነት፣ ነጻነት፣ ወንድማማችነት፣ የሰብአዊ መብት መከበር፣ የጋራ ብልጽግና፣ ፍትሐዊ የሆነ የሥልጣን አጠቃቀምና ጥቃትን መከላከል የመሳሰሉ መርሆዎች (guiding principles) ናቸው። እነዚህ መርሆዎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያላቸው ናቸው። ስለዚህም አንድ ክርስቲያን ፕሮግራሙ ግልጽና በእነዚህ መርሆዎች

ላይ የተመሠረተ፣ የተነሣበት ዓላማና ግቡ፣ አካሄዱም ከክርስትና እምነትና ሥነ ምግባር ጋር በማይቃረን ፓርቲ ውስጥ አባል በመሆን ብዙ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ሊሠራ ይችላል። ነገር ግን ዓለማችን ከላይ ያየናቸውን መርሆዎች ለይስሙላ ብቻ በያዙ፣ ዘረኝነትንና ወገናዊነትን በሚያራምዱ፣ በሙስናና በብልሹ አሠራር የተበከሉ ፓርቲዎች የሚገኙባት ስፍራ በመሆኗ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ክርስቲያኖች በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉበት ሁለተኛው መንገድ የክርስቲያን ፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚመኘውን ፍትሕን፣ ሰላምን፣ ታማኝነትን፣ ፍቅርን መሠረት ያደረጉ የክርስቲያን ፓርቲዎች ቢቋቋሙ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ ፓርቲዎች በአውሮፓ ውስጥ እንደ ጀርመን፣ ሆላንድ፣ ጣሊያንና ፈረንሳይ፥ እንዲሁም በደቡብ አሜሪካ በአንዳንድ አገሮች ውስጥ ተቋቁመው የነበር ሲሆን፥ በሩሲያም ኮሚኒዝም ሊወድቅ በተቃረበበት በ1989 (እ.ኤ.አ) <<Christian Democratic Union of Russia>> በመባል የሚታወቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያደገ ፓርቲ ተቋቁሞ ነበር። የእነዚህ ክርስቲያናዊ ፓርቲዎች እንዲቋቋሙ አስገዳጅ የነበረው ሁኔታ በአንድ በኩል፣ በየአገሮቹ የነበሩት መንግሥታት ጨቋኝና በሞራል ዝቅጠት ውስጥ የነበሩ መሆንና ከእነርሱ ለመላቀቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማርክሳዊ ፍልስፍና (Marxist Ideology) እየተስፋፋ በመምጣቱ ያሳደረው ተጽዕኖና ይህንንም ለመቋቋም ነበረ።

ወደ አገራችን የአሁን ሁኔታ ስንመጣ፣ የክርስቲያን ፓርቲ የማቋቋምን ጉዳይ በአሳብ ደረጃ እንደ አማራጭ ለማየት ካልሆነ በስተቀር ወደ ድርጊት ለመግባት የማያስችሉ እንቅፋቶች አሉብን። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው። በመጀመሪያ በአሁኑ ሰዓት የምንመራበት የአገራችን ሕገ መንግሥት ፓርቲዎች በሃይማኖት መሥመር እንዲቋቋሙ አለመፍቀዱ ዋነኛው ነው። ይህ ሁኔታ የሚለወጥ ቢሆን እንኳ ተያይዞ የሚታይ፣ በአገራችን ውስጥ ክርስቲያናዊ ፓርቲ ማቋቋምን ጠቃሚ የማያደርግ ሌላ የጎላ ችግር አለ፤ ይህም አገራችን የተለያዩ ሃይማኖቶች የሚስተናገዱባት የመሆኗ ጉዳይ ነው። ከላይ እንደ ምሳሌ የተጠቀሱት አገሮች የአንድ ሃይማኖት

ተከታይ የሆኑ ወይም በአንድ አገር አቀፍ ቤተ ክርስቲያን (National Church) የታቀፉ ሕዝቦች የነበሯቸው በመሆኑ ክርስቲያናዊ ፓርቲዎች ለማቋቋም ብዙ ያልተቸገሩ ሲሆን፤ አገራችን ግን የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚከተል ሕዝብ ያላት በመሆኗ ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች ቢቋቋሙ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል። ከዚህም ባሻገር በክርስቲያን ፓርቲው ላይ አንዳች ጉድለት ቢገኝበት ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች የሚሰነዘረው ነቀፌታ ፓርቲውን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በክርስትናም ላይ እንዲያነጣጥር መንገድ የሚከፍት መሆኑና ክርስቲያኖች በአንድ ፓርቲ ሥር ብቻ መሰባሰባቸው በሌሎች ጠቃሚ ፕሮግራም ባላቸው ፓርቲዎች ውስጥ በመግባት ጨው የመሆን ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ እንቅፋት መሆኑ ተያይዘው የሚጠቀሱ ሌሎች ችግሮቹ ናቸው።

## ሠ. ለፖለቲካ ሥልጣን በመወዳደር

በዚህ መንገድ በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ለሁሉም የማይሆንና ሊሳተፉ የሚፈልጉ ክርስቲያኖችም ብርቱ ጥንቃቄ ሊያደርጉበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ከዚህም በላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ከራሳቸው ጋር ሊያገናዝቧቸው የሚገቡ መመሪያዎች አሉ። የእነዚህም መመሪያዎች መሠረት የአምላካችን ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ያሉትን፤ በእግዚአብሔር ተመርጠው ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የመጡትን ከሙሴ ጀምሮ በእስራኤል ላይ የተሾሙ የብዙ መሳፍንትንና ነገሥታትን ታሪክ ስንመለከት፤ እግዚአብሔር ካስታጠቃቸው ጥበብና ማስተዋል የተነሣ ተሹሞ በሄደበት በግብፅ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የበቃውን ዮሴፍን (ዘፍጥ. 41፡37)፤ ምርኮኛ ሆኖ በሄደበት በባቢሎን በከፍተኛው የሥልጣን ቦታ ላይ የተቀመጠውንና በተከታታይ በነገሡ የባቢሎን፤ የፋርስና የሜዶን መንግሥታት ውስጥ ከፍ ከፍ የተደረገውን ዳንኤልንና (ዳን. 2፡48፤ 5፡29፤ 6፡1-3፤ 28) ሌሎችን ለከፍተኛ ሥልጣን የበቁትን ሰዎች ታሪክ ስንመለከት፤ አንድ በፖለቲካ ውስጥ ሊሳተፍ ለሚወድ ክርስቲያን አስቀድሞ ሊገነዘባቸው የሚገቡ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነገሮችን እናገኛለን።

1. እግዚአብሔር ለዚህ ነገር እንደ መረጠው በትክክል መገንዘብ አለበት። ለማንኛውም ተግባር የሚነሣ ክርስቲያን መነሻ ምክንያቱ

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ የገዛ ስሜቱ ወይም የሰዎች ግፊት መሆን አይገባውም።

2. ከሚይዘው የፖለቲካ ቢሮ (political office) ጋር ተመጣጣኝነት ያለው እውቀት እንዳለው ማረጋገጥ አለበት። ያለ እውቀት የሚደረግ ነገር ውጤት አያመጣም።

3. በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነትና መደገፍ እጅግ የጸና፣ ቃሉን በሚገባ የሚያውቅ፣ በሕይወቱና በኑሮውም ላይ ነቀፌታ እንዳይኖር የሚጠነቀቅ ሰው ሊሆን ይገባዋል።

4. የፖለቲካ ሥልጣን ሕዝብን ማገልገያ እንጂ ለግል ክብርና ዝና መገልገያ መሣሪያ መሆን እንደማይችል የገባው መሆን አለበት።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን እንደ ቅድመ ሁኔታ ከራሱ ጋር አዛምዶ በማየት ተገቢውን ግንዛቤ የጨበጠ ክርስቲያን ለየትኛውም የሥልጣን እርከን ቢታጭ ወይም በአካባቢም ሆነ በክልል ወይም በአገር አቀፍ በሚደረግ ምርጫ ቢወዳደር እግዚአብሔር ሊጠቀምበት ይችላል።

## 3. የፖለቲካ ሥልጣን የያዘ ክርስቲያን ሊከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች

ሀ/ ባለበት የፖለቲካ ሥልጣን የተጣለበትን ኃላፊነት፣ በእግዚአብሔር ቃልና መንግሥት በደነገጋቸው የሥነ ምግባር መርሆዎችም ላይ ተመርኩዞ በብቃት ለመተግበር መጣር አለበት። የተደነገጉት የሥነ ምግባር መርሆዎች ተጠያቂነት፣ ታማኝነት፣ ግልጽነት፣ ቅንነት፣ አለማዳላት፣ ምሥጢር ጠባቂነትና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ እነዚህም ከክርስትና መርሆዎች ጋር የሚጣጣሙ እንጂ ተፃራሪ ባለመሆናቸው በክርስትናው ጸንቶ ላለ አማኝ አስቸጋሪ አይሆኑም።

ለ/ ከላይ እንደ ተጠቀሰው አንድ ክርስቲያን ለተቀበለው የሥልጣን ቦታ ተፈላጊ የሆነው እውቀት ሊኖረው የግድ ነው። በእስራኤል ላይ አለቆች ሊሆኑ በሙሴ የተመረጡት ሰዎች ዋነኛ መመዘኛ እውቀታቸው ነበር (ዘፀ. 18፥25)። ከእውቀት ማነስ የተነሣ ኀላፊነቱን መወጣት ከማይችል አማኝ ይልቅ ኀላፊነቱን በእውቀት የሚወጣ አማኝ ያልሆነ ሰው ጠቃሚ ሥራ መሥራት ይችላል። ከትምህርትና ከልዩ ልዩ ሥልጠና እንዲሁም ከልምድ የሚገኝ እውቀት ኃላፊነትን

በተገቢው መንገድ ለመወጣት አስፈላጊ መሆኑ ባይካድም ብቻውን ግን በቂ አይሆንም። ከዚህ በተጨማሪ ከእግዚአብሔር እጅ የሚገኘውን ጥበብና ማስተዋል ተግቶ መሻትና መለመን አስፈላጊ ይሆናል (ያዕ. 1፡5፤ ምሳ. 2፡3–4፡6)።

«ከቀይ እንቁ ትበልጣለችና፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም» በሚል መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሞግሳት ጥበብ (ምሳ. 8፡11)፤ ነገሥታት በተገቢው መንገድ እንዲያስተዳድሩ፤ ሹማምንትም በጎ ሕግ እንዲያወጡ የምትረዳቸው፤ አለቆችንም ሆነ መኳንንትን እንዲሁም ፈራጆችን የምታግዛቸው እንደሆነች ቃሉ ይነግረናል (ምሳ. 8፡15–16)። አይሁዳውያኑ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ በባቢሎን ግዛት ከነበሩት ጥበበኞች ሁሉ በአሥር እጥፍ በልጠው የመገኘታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር እጅ ከተቀበሉት ጥበብ የተነሣ እንደነበር እናያለን (ዳን. 1፡17–20)። የሰሎሞንን ጥበበኝነት አባቱ ዳዊት ደጋግሞ የመሰከረለት ቢሆንም (1ኛ ነገ. 2፡6፤ 9)፤ ከእግዚአብሔር እጅ የሚገኘውን ጥበብና ማስተዋል ግን ተገቶ የፈለገና በሙላት የተቀበለ ንጉሥ ነበር። ስለዚህም ኀላፊነትን በማስተዋልና በብቃት ለማከናወን በልግስና ከሚሰጥ እግዚአብሔር እጅ ጥበብን መለመን (ያዕ. 1፡5) አስፈላጊም አስተዋይነትም ነው።

ሐ/ በያዘው የፖለቲካ ሥልጣን ሊገለገሉ የሚገባቸውን ሁሉ ያለአንዳች አድልዎ፤ በእኩል ማገልገል ይገባዋል። በሀብት፤ በዘር፤ በጎሳ፤ በሃይማኖት፤ በዝምድናና በቅርበት ወይም በማንኛውም ሌላ መለኪያ በሰው መካከል የሚደረግ አድልዎ ኃጢአት መሆኑንና እንደ ሕግ ተላላፊ የሚያስወቅስ መሆኑን ተገንዝቦ (ያዕ. 2፡9)፤ ከአድሎአዊነትና ለወገኔ ይጠቅማል ከሚል የወገንተኝነት መንፈስ መራቅ አለበት (ፊልጵ. 2፡3)። ይልቁንም ለሌሎች የሚጠቅመውን ሁሉ በማድረግ፤ በትሕትናና ዝቅ በማለት ሁሉን በእኩል ማገልገል (2፡3–4) ተግባሩ ማድረግ ይገባዋል። ይህም ተከታዮቹ ነን የሚሉ ሁሉ የክብራቸው ምንጭ ትሕትናቸው፤ የትልቅነታቸውም ምንጭ ዝቅታቸው መሆን እንደሚገባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማርቆስ ወንጌል 10፡43–44 ካስተማረው ጋር ይስማማል።

መ/ ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የመጣ ክርስቲያን የተሰጠውን ኀላፊነት በብቃት ለመወጣት መጣር እንጂ የያዘውን ሥልጣን ለእምነቱ

ማራመጃ መሣሪያ አድርጎ ከመጠቀም መቆጠብ ይገባዋል። ይህ፣ ከተሰጠው የሥልጣን ኀላፊነት ውጭ መሄድን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፥ ከማያምኑት ወገን ከበሬታን ሳይሆን ሐሜትንና ጥላቻን አትርፎ ከጠቀሜታው ይልቅ የሚያስከትለው ጥፋት ሊያመዝን ይችላል። ከዚህ ይልቅ በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በታነጸ መልካም ሥራ ቢጸና፣ እምነቱንም በትክክል ቢኖርበት፣ የሚገለጠው ብርሃን የመሆን አገልግሎት ለእግዚአብሔር የበለጠ ክብርን ያመጣል (ቲቶ 3፡8፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡12፤ ማቴ. 5፡16)። ዮሴፍና ዳንኤል ለእግዚአብሔርም ሆነ ለራሳቸው ከበሬታን ያስገኙት እምነታቸውን ስለሰበኩት ሳይሆን ስለኖሩት ነበር።

ሠ/ አንድ ክርስቲያን ባለው የሥልጣን ኀላፊነት መሠረት ሊተገብረው ወይም ሊወስነው ያለ ጉዳይ ቢኖር፣ ይህም ጉዳይ ከመልካም ኅሊናው ጋር የሚጋጭበት፣ የእምነት አቋሙንም የሚያናጋበት ሆኖ ቢያገኘውና ይህንንም ሁኔታ በተገቢው መንገድ ለማስተካከል ዕድል ቢያጣ ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዱ መልቀቁ (resign) ተገቢ እርምጃ ይሆናል። ፖለቲካ ከውስጥም ሆነ ከውጭ በሚነሡ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምክንያት ተለዋዋጭ ባሕርይ ያለው ሲሆን፥ ክርስትና እምነት ግን ጸንቶ የሚኖር በመሆኑ፣ የፖለቲካ ሂደቶች በእምነቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርጉ መፍቀድ የለበትም። ይልቁንም፣ በፖለቲካ አመለካከቱም ሆነ በአቋሙ ላይ እንዲሁም በሚተገብራቸውም ሆኑ በሚወስናቸው የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የእምነቱ ተጽዕኖ አስፈላጊ ይሆናል።

እምነትና ፖለቲካ በእኩልነት መቀመጥ አይችሉም። እምነት ፊተኛና የበላይ መሆን ስለሚገባው ለፖለቲካ ትርፍ ወይም ለሥልጣን ወንበር ሲባል እምነትን ለድርድር ማቅረብ ለአንድ አፍታ እንኳን ማሰብ አይገባም። በመሆኑም የእምነት ሕይወቱን የሚጎዳ ሁኔታ የገጠመው፣ በዚህም መነሻነት ሥልጣኑን የመልቀቅ ውሳኔ ላይ የደረሰ ክርስቲያን ይህንን ውሳኔውን ግልጽና ጥንቃቄ በተሞላበት እንዲሁም ምሥጢር በሚጠበቅበት መንገድ ማከናወን ይጠበቅበታል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን መመሪያው አድርጎ መያዙ ወደ ፖለቲካ ውስጥ ለሚገባ ለአንድ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ ነው ቢባልም፥ ሙሉ በሙሉ መሳካትን ያመጣል ማለት ግን አይደለም። የፖለቲካ

መድረክ ብዙ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የሚከሰቱበትና ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው በመሆኑ የቃሉን ምሪት መፈለግ፣ የእግዚአብሔርን ፊት ተግቶ መሻትና «እንደ እባብ ልባም» ሆኖ መገኘት ከብዙ አደጋ ይጠብቃል።

## በፖለቲካ ውስጥ ለሚሳተፍ አማኝ ከቤተ ክርስቲያን ሊሰጠው የሚገባ ድጋፍ

ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ውሳኔዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆንና የመንግሥትም ሆነ የሌላ ማንኛውም ወገን የፖለቲካ ፕሮግራም መጠቀሚያ መሣሪያ መሆን እንደማይገባት አስቀድመን ተመልክተናል። ሆኖም ምእመናን በአገራቸው የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ዜግነታቸው በሚፈቅድላቸው መንገድ ሁሉ ለመሳተፍ እንዲነሣሡ (influence) በማድረግ ሕዝባችንን ቀፍድዶ ከያዘው የፖለቲካ ችግር ለማላቀቅ በሚደረገው ትግል ውስጥ ተገቢ ስፍራ እንዲኖራቸው የማድረግ ሚና መጫወት ትችላለች። አሁን ግን በስፋት እንደሚታየው፣ ኅብረተሰባችን የገባበትን ሁለገብ ችግር እንደሌለ መቁጠር ወይም ስለ ችግሩ አለማንሣትና በዝምታ መመልከት ችግሩን አያስቀረውም ወይም አያስወግደውም። ይልቁንም ገለልተኛ የሆንንባቸው፣ በዝምታም የምናያቸው በውጭ ያሉ ችግሮች ምንም ዐይነት የቤተ ክርስቲያን አጥር ሳያግዳቸው ጥሰው በመግባት ምእመኑን እስከ መበተን እየደረሱ እንደሆነ እያየን ነው። ከመንግሥት ፖለቲካ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የፖለቲካ (church politics) እርሾ እጅግ እየኮመጠጠ የመጣበት፣ ጎሰኝነት፣ ሙስና፣ መገፋፋትና አለመቻቻል የቤተ ክርስቲያን ገጽታ እየሆኑ የመጡበት ጊዜ አሁን ሳይሆን አይቀርም። ይህ የውስጥ ገጽታ ካልተለወጠ ደግሞ የተቃና አገልግሎት ማገልገል ለቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ ይሆናል።

የውስጥ ገጽታን የመለወጥ ሂደት ደግሞ በውጭ ያለውንም ለመለወጥ ከመዘጋጀት ጋር ካልተቀናጀ ውጤቱ አመርቂ አይሆንም። ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው ለመልካም ውጤት መብቃት ብቻ ሳይሆን፥ የጨለመውንና ጣእም ያጣውን አካባቢያቸውንም መለወጥ ይችላሉ። ይህንን በልበ ሙሉነት ማለት ቢቻልም፣ አሁን ግን ያለው፣ እግዚአብሔር እውቀትን እንደሚጠላ አድርጎ የማሰብና ከእውቀት

መሸሸን እንደ ጽድቅ መንገድ አድርጎ የመቁጠር የአላዋቂነት አባዜ ተለውጦ አማኞች በሁሉም የሙያ ዘርፍ ብቁ ተወዳዳሪ (competent) ሆነው ለመቅረብ መነሣሣት አለባቸው። ይህ እውን እንዲሆን፣ አባሎቻቸው በየትኛውም መስክ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ የሚያበቃቸውን ተገቢ እውቀት ለመጨበጥ እንዲተጉ መምከርና ማነሣሣት ትልቁ ኃላፊነት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትከሻ ላይ ወድቋል። እነዚህ ወንድና ሴት የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው በየተሰማሩበት ሙያ ብርሃን የሚፈነጥቁ፣ ጣእም ላጣውም ዙሪያ ገባ ሕይወት ጨው በመሆን የሚያጣፍጡና ታላቅ የለውጥ ኀይል በመሆን ቀዳሚውን ረድፍ መያዝ የሚችሉ።

በፖለቲካውም መስክ እንዲሁ የለውጥ ኀይል መሆን የሚችሉ፣ በአገር ጉዳይ ላይ ልባቸው የሚቃጠል፣ በክርስትና እውነት የዘቀጠውን የፖለቲካ አየር መለወጥ እንደሚቻል የሚያምኑ፣ የፍትሕ ጉዳይ የሚያንገበግባቸው አማኞች አሉ። እነዚህን ለይቶ የማወቅ፣ ያላቸውንም ራእይ በቃሉ ፈትሾ የማበረታታት፣ አስፈላጊውንም የቃሉን ትጥቅ የማስታጠቅና በጸሎት የማገዝ ድርሻና ኀላፊነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው። ከዚህ ይልቅ እስከ አሁን እንደሆነው፣ መሪዎቻችን ሁኔታዎችን በዝምታ የማየት መንገድ የሚመርጡ ከሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ሊኖር የሚገባውን የአማኞች ድርሻ ችላ በማለት፣ ስለ አገራችን ከማዘንና ከንፈር ከመምጠጥ ያለፈ ተግባር ሳይኖረን ይቀራል። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የከፈተልንን በር በራሳችን ቸልተኝነት እስከ ወዲያኛው ልንዘጋው ዕድሉን ደግመን ወደማናገኝበት ሁኔታ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን። ይህ ደግሞ "በፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ እምቢተኛ የሆኑ መልካም ሰዎች ዕጣ ፈንታ፣ በክፉ ሰዎች መገዛት ነው" ("The fate of good men who refuse to become involved in politics, is to be ruled by evil men.") የሚለውን የቆየ አባባል ያሳስበናል።

# ማጠቃለያ አስተያየት

ማንም ሰማያዊ ብርሃን የበራለት ሰው እንደሚረዳው፣ አገራችንን አንቆ የያዘው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ውድቀት መነሻ ምንጩ መንፈሳዊ ውድቀትን ተከትሎ የነገሠው የሞራል ልሽቀት ነው። እንደ እኔ እምነት ለዚህ የከፋ የሞራል ውድቀት መድኀኒት ለመሆን የሚችል ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ ሊያመጡ የሚችሉት ሰዎችን እግዚአብሔር እየፈለገ ያለበት ሰዓት ዛሬ ይመስለኛል። ለዚህ ታላቅ ጥሪ ደግሞ የአማኞች ምላሽ አማራጭ የሌለው ነው። ምክንያቱም አማኞች ወደ ፖለቲካው ዓለም ይዘው መምጣት የሚችሉት ልዩ የሆነ የውስጥ ሀብትና (resource) ሰማያዊ ትጥቅ አላቸው።

በፖለቲካ ሥልጣን አለአግባብ መጠቀም የሚመጣው ሰዎች ካለባቸው የውስጥ ባዶነት የተነሣና ይህንንም ባዶነት ለመሙላት በሚደረግ የበለጠ ሥልጣን፣ የበለጠ ሃብትና ዝና በማግበስበስ የበላይ ሆኖ ለመታየት ከሚደረግ ግለኛ ሩጫ የተነሣ ሲሆን፥ ይህም መሻት ለብዙ ብልሹ አሠራር ይዳርጋቸዋል። ክርስቲያኖች ግን ይህ የውስጥ ባዶነታቸው በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ በመሆኑ፣ በያዙት ሥልጣን ላይ አገልጋይ እንጂ የበላይ እንደሆኑ ሊያስቡ እንደማይገባቸው፣ የሌሎችን ጥቅም እንጂ ለራሳቸው ታይታና ዝና ሊሮጡ እንደማይገባቸው ከቃሉ ስለሚረዱ የፖለቲካ ሥልጣንን በተገቢውና በተሻለ መንገድ መያዝ ይችላሉ። ይህ ማለት ግን ለአማኞች ነገር ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆናል ማለትም አይደለም፣ ዋጋ የሚያስከፍሉ አደገኛ ሁኔታዎችም ሊከሰቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርብናል። በየዕለቱ ራሳቸውን መፈተሽና መመዘን ካልቻሉ ሌሎች በወደቁበት አዘቅት እነርሱም ሊወድቁ ይችላሉ።

ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የሚመጡ ወንዶችና ሴቶች አማኞች በመንግሥት ውስጥ ያላቸው ድርሻ መተኪያ የሌለው እንደሆነ በመገንዘብ የፖለቲካ ሕይወታቸውን የክርስቲያን ተግባራቸው አካል አድርገው መቁጠር ይገባቸዋል። ራሳቸውንና እግዚአብሔር በውስጣቸው ያስቀመጠውን ሀብት በዙሪያቸው ላሉት የሰው ልጆች ጥቅም የሚሰጡ ክርስቲያኖች የአጋፔ ፍቅር (Agape Love) የገባቸውና ከማንም በላይ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ናቸው።

# BIBLIOGRAPHY

Barth, Karl. *Community, State, and Church: Three Essays.* New York: Doubleday, 1960.

Bennett, John C. *Christians and the State.* New York: Charles Scribner's Sons, 1958.

Buzzard, Lynn and Paula Cambell. *Holy Disobedient: when Christians must resist the state.* Mchigan: Servant Books, 1984.

Colson, Charles. *Kingdoms in Conflict.* Grand Rapids, MI: W. Morrow and Zondervan Publishing House, 1987.

Dow, Graham. *The Local Church's Political Responsibility.* Ridley Hall RD Cambridge: Grove Books,1980.

Edsimoe, John. *God and Caesar: Christian Political Action.* Westchester, Ill: Crossway Books,1984.

Gideomal, Ram. *How would Jesus Vote?: what to look for in your national leaders.* UK: Monarch Books, 2001.

Haselbarth, Hans. *Christian Ethics in the African Context.* Nairobi, Kenya: Uzima Press, 1976.

Kudadjie, J.N. and R.K. Abagye Mensah. *The Christian and National Politics.* Accra: Asempa Pub.,1998.

McQuilkin,Robertson. *An Introduction to Biblical Ethics.* Weaton, Illinois: Tyndale House of Publishers, 1989.

Okullu, Henry. *Church and State in Nation Building and Human Development.* Cincinnati: Forward Movement Publications, 1987.

Okullu, Henry. *Church and Politics in East Africa.* Nairobi, Kenya: Uzima Press, 1974.

Piligrim, Walter E. *Uneasy Neighbors: Church and State in the New Testament.* Mineapolis, MN: Fortress Press, 1999.

Stott, John R. W. *Issues Facing Christians Today.* Great Britain, 1990.

Taylor, J. V. *Christianity and Politics in Africa*. London: Penguin Books, 1957.

Tillman, William M., Jr.,editor. *Understanding Christian Ethics*. Nashville, Tennessee: Broadman Press, 1988.

Tillman, William M. *Christian Ethics: a premiere*. Nashville, Tennessee:Broadman Press, 1986.

Yoder, John Howard. *The Christian Wittness to the State*. Newton, Kan: Faith and Life Press, 1964.

ወንድም ኤልያስ በቀለ «ክርስቲያን እና ፖለቲካ» በሚል ርእስ ያዘጋጀው አነስተኛ መጽሐፍ በአማኞች አካባቢ በቂ ትኩረት ያልተሰጠውንና አማኞችም በተቻለ መጠን የሚሸሹትን ርእስ ለመዳሰስ የሞከረ ነው:: ጽሑፉ የውይይትን አሳብ በአማኞች ዘንድ የሚጭር ከመሆኑ የተነሣ በዚህ ርእስ ሌሎች መጻሕፍት እንዲጻፉና ውይይቶች እንዲካሄዱ የሚያበረታታ ነው::

ስለሺ ከበደ (መጋቢ)
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ኅብረት
ተባባሪ ዋና ጸሐፊ

ይህች አነስተኛ መጽሐፍ ብዙ ቁም ነገሮች አሉባት:: እስከ ዛሬ ድረስ ማንም ያልደፈረውን ርእስ አንሥታ ትሞግተናለች:: አንዳንዴም በብርቱ እየወቀሰች በአገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ዝምታን የመረጥነው ለምን እንደሆነ ትጠይቀናለች:: ዝምታን መምረጡም አግባብ እንዳልሆነ ትመክረናለች:: ጸሐፊው በዚህ ርእስ ላይ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት መነሣቱ እጅግ ያስመሰግነዋል::

ምኒልክ አስፋው

---



አቶ ኤልያስ በቀለ ሀ/ማርያም በሙዚቃ ሙያ ውስጥ ተሰማርተው እያሉ በ1983 ዓ.ም. ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ:: ከብዙ ዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ ትምህርት ዓለም ተመልሰው በ1984 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመግባት በማታው ክፍለ ጊዜ ትምህርታቸውን በመከታተል በፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት (PSIR) የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በ1991 ዓ.ም አገኙ:: በ1992 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የሥነ መለኮት ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት (Ethiopian Graduate School of Theology) በመግባት በመጽሐፍ ቅዱስ እና ሥነ መለኮት ጥናት የማስተርስ ዲግሪያቸውን (MABTS) በ1993 ዓ.ም ተቀብለዋል::

አቶ ኤልያስ ባለትዳር እና የሦስት ልጆች አባት ሲሆኑ፣ አባል በሆኑበት በዓለም አቀፍ የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን (IEC) የአምልኮ ጓድ ውስጥ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

POLITICS

Christian and Politics

Printed by SIM Press